ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 267 ግንቦት 27 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

pepsi

## በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና ተጽዕኖ ፈጣሪ ስታርትአፖችን ለማፍራት በቅንጅት መሥራት ይገባል

### - ኢትዮጵያ የመላው አፍሪካ ስታርትአፕ ውድድርን ለማዘጋጀት ተመርጣለች

ሄለን ወንድምነው



አዲስ አበባ፡- በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና ተጽዕኖ አድራጊ የቴክኖሎጂ ሥራ ፈጣሪዎችን (ስታርትአፖችን) ለማፍራት በቅንጅት ልንሠራ ይገባል ሲሉ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ ገለጹ። በመጪው ዓመት ኢትዮጵያ የመላው አፍሪካ ስታርት አፕ ውድድርን ለማዘጋጀት መመረጧን ተጠቁሟል፡፡

ኢትዮጵያ የመላው አፍሪካ ስታርት አፕ ውድድርንና ሽልማትን ጥቅምት 2017 እንድታዘጋጅ መመረጧ ተመላክቷል።

የግሎባል ስታርትአፕ አዋርድስ አካል የሆነው ኢትዮጵያ ስታርትአፕ አዋርድስ መክፈቻ መርሐ ግብር ትናንት ተካሂዷል።

በመክፈቻ መርሐግብሩ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ እንደገለጹት፤ መንግሥት የሀገሪቱን የስታርት አፕ ሥነ ምህዳርና ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ ከፍተኛ ርብርብ እያደረገ ነው።

በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ተጽዕኖ መፍጠር የሚችሉ በቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረቱ ፈጠራዎች (ስታርትአፖችን) የማፍራት፣ የዓለም ገበያን የማመቻቸትና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ሀብት የማፍራት ሥራን በቅንጅት መሥራት እንደሚገባ አስታውቀዋል።

ስታርትአፖች ለማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሁለንተናዊ እድገት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ። በዚህም የተለያዩ ሀገራት ከኢኮኖሚ መሪነት

በዓለም አቀፍ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የፖለቲካ ፓርቲዎች በምክክሩ በመሳተፍ ታሪካዊ ዐሻራቸውን ማኖር አለባቸው

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡- በሀገራዊ ምክክሩ የማይሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምክክሩ በመሳተፍ ታሪካዊ ዐሻራቸውን ማኖር እንዳለባቸው የአዲስ አበባ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ምዕራፍ ተሳታፊዎች ገለጹ።

የኢዜማ ተወካይ አቶ ግርማ ሰይፉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገራዊ ምክክሩ የማይሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምክክሩ መሳተፍ አለባቸው። በመሳተፍም ለሀገራቸውም ሆነ ለትውልዱ ታሪካዊ ዐሻራቸውን ማኖር ይጠበቅባቸዋል።

ምክክሩ በየትኛውም ሂደት ላይ ቢሆንም ባለበት ደረጃ መቀላቀል እንዳለባቸው ተናግረው፤ ይህንን ሳያደርጉ ቀርተው በታሪክ አጋጣሚ የተገኘው የሀገራዊ ምክክር እድል ሳይጠቀሙበት ማለፍ እንደሌለበት አመላክተዋል ።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

Development Bank of Ethiopia

## ባንኩ የተበላሸ የብድር ምጣኔውን ዝቅ እንዲያደርግ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ያለበትን ከሰባት በመቶ በላይ የተበላሸ የብድር ምጣኔ ዝቅ እንዲያደርግ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የ2016 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወር አፈፃጸሙን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

ባንኩ የተበላሸ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ከበልግ እርሻ ከ63 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል

ታደሠ ብናልፈው



አዲስ አበባ፡- ዘንድሮው ከበልግ እርሻ ከ63 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት እየተሠራ መሆኑን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈፃሚ አቶ ከበደ ላቀው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016 ያለው የዝናብ ስርጭት ለበልግ እርሻ ተስማሚ ከመሆኑ ባለፈ የግብዓት አቅርቦቱ የተሟላ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ከዘንድሮው የበልግ እርሻ ከ63 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል፡፡

በ2016 ሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በበልግ እርሻ በማልማት መታቀዱን አስታውሰው፤ እስካሁን ከሶስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ሄክታር መሬት የማዘጋጀት ሥራ ተከናውኗል ብለዋል፡፡

የ2016 የበልግ ወቅት ያለው የዝናብ ስርጭትና የአየር ሁኔታ ለግብርና ሥራው አመቺ ከመሆኑም ባለፈ በአብዛኛውን የሀገሪቱ ክፍል ያካለለ መሆኑን አንስተዋል።

አርሶ አደሩም እየዘነበ ያለውን ዝናብ በመጠቀም

ከበልግ እርሻ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ኤኤምጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
AMG Steel Factory



Tel:- 0940 505050 – 0940 606060 – 0940 909090 – 0940 808080 -0920 656565



# የቀዳማዊት እመቤት ጽሕፈት ቤት ከጉድ ኔበርስ ጋር በጋራ ለመስራት ስምምነት አደረጉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የቀዳማዊት እመቤት ጽሕፈት ቤት ከጉድ ኔበርስ ዓለም አቀፍ በጎ አድራጎት ድርጅት ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል።

ዋናው መቀመጫውና የተመሠረተበት ሀገር ደቡብ ኮሪያ ከሆነው ጉድ ኔበርስ ዓለም አቀፍ በጎ አድራጎት ድርጅት ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ስምምነት መደረሱን የቀዳማዊት እመቤት ጽሕፈት በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት አስታውቀዋል።

ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው በመልዕክቱ እንደገለጹትም፤ ከበጎ አድራጎት ድርጅቱ ጋር በፅሕፈት ቤታቸው እየተከናወኑ ያሉ የልማት ሥራዎችን ለመደገፍ እና በጋራ ለመሥራት የሚያስችላቸውን ውይይት አድርገዋል።

በውይይቱም ወደ ሥራ የሚያስገባ የመግባቢያ ሰነድ መፈራረማቸውን ነው ቀዳማዊት እመቤቷ የጠቆሙት፡፡

በተያያዘ ኮሪያ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን በትምህርት እና በመምህራን ሥልጠና ዘርፍ እንደምትደግፍ አስታውቃለች።

የትምህርት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ከኮርያ ሪፐብሊክ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የትምህርት ሚኒስትር ሊ ጁ ሆ ጋር ተወያይተዋል።

በዚህም በከፍተኛ ትምህርት፣ በአጠቃላይ ትምህርት እና በመምህራን ሥልጠና ዘርፍ ኮሪያ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን እንደምትደግፍ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የትምህርት ሚኒስትሩ ገልፀዋል።

በውይይታቸውም በትምህርት ዘርፍ ስለሚኖረው ትብብር አንስተው መምከራቸውን የትምህርት ሚኒስቴር መረጃ ያመላክታል።

# በመጪዎቹ አስር ቀናት

## አብዛኛው የሀገሪቱ ወንዞች ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት ይኖራቸዋል

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በመጪዎች አስር ቀናት በሀገሪቱ በሚገኙ በአብዛኛው የወንዞች ተፋሰሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚኖራቸው የኢትዮጵያ ሜቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

ኢንስቲትዩቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤በመጪዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛው ዓባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ፣ጊቤ፣ አፋር ደናክል፣ የላይኛው እና የመካከለኛው የስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው ዋቢ ሸበሌ እና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም በግብርናው ዘርፍ ከሚኖረው ጥቅም ባለፈ ለኃይል ማመንጫ ግድቦች አወንታዊ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ እርጥበታማው የአየር ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው መረጃው አመልክቷል፡፡

ይህ የዝናብ ስርጭት በእርሻ ሥራ ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖ ሲታይ በተለይ በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው ተገልጿል፡፡ ይህም ሁኔታ አስቀድመው ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እና ለጓሮ አትክልቶች ከፍተኛ ጠቀሜታ እንደሚኖረው መረጃው አብራርቷል፡፡

በመጪው የሰኔ ወር ዝናብ ሰጪ መረጃዎች የሚያመላክቱ ሲሆን በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች አንፃራዊ ጥንካሬ እንደሚኖራቸው የአሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም በተለይም በምዕራብ አጋማሽ ኢትዮጵያ የዝናቡ በመጠን ሆነ በስርጭት የተሻለ እንደሚሆን የሚጠበቅ እንደሚሆን ተመላክቷል፡፡

በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ከሚጠናከሩ ዳመናዎች ላይ በመነሳት ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ትንበያው መረዳት መቻሉን ተጠቁሟል፡፡

ከሰኔ 11 እስከ 20 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በደቡብ ምዕራብ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛው አካባቢዎች ላይ ዝናብ ሰጪ የሜትዎሮሎጂ ገፅታዎች እየጠነከሩ ይሄዳሉ ያለው ኢንስቲትዩቱ፤ በአንፃሩ በሰሜን እና በሰሜን ምስራቅ ላይ አልፎ አልፎ ከሚኖረው መጠነኛ ዝናብ በስተቀር ደረቅ እና ሞቃታማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን ተጠቁሟል፡፡

# ዩኒቨርሲቲው የመንግሥት ሠራተኞች ሥራ የመፈጸም አቅማቸውን የማሳደግ ሥራ እየሰራ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውጤታማ እንዲሆኑ ሠራተኞች ሥራ የመፈጸም አቅማቸውን የማሳደግ ሥራ እየሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ «የሕዝባዊ ተቋማት ለውጥና ልማት» በሚል መሪ ቃል ዘጠነኛውን ዓመታዊ የምርምር ጉባዔ ትናንት አካሂዷል። የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ፍቅሬ ደሳለኝ ለጋዜጠኞች እንደገለጹት፤ ጉባዔው በሀገራችን ባሉ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ስላሉ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸውን በተመለከተ ጥናቶችን ያካሂዳል። የዩኒቨርሲቲው ዋና ተልዕኮ በመንግሥት ተቋማት፣ ሠራተኞች፣ በመንግሥት አጠቃላይ አወቃቀርና አሠራር ላይ የሚታዩ ችግሮች ላይ ጥናት በማካሄድ ችግሮችን የመለየትና አገልግሎቶች እንዲሻሻሉ የማድረግ ሥራ ይሠራል ብለዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ በመንግሥት ተቋማት የሚሠሩ ሠራተኞች የተሰጣቸውን ሥራ የመፈጸም አቅማቸውንና ችሎታቸውን የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ነው።

በተማሩባቸው ተቋማት አስፈላጊውን ክህሎቶች ሳያገኙ በተለያዩ ተቋማት የሚሠሩ ሠራተኞች መኖራቸውን ገልጸው፤ ይህን ችግር ለመቅረፍና የሠራተኞችን ብቃት ለማሳደግ የሚያስችል የጥናቶች ውጤቶች ለሚመለከታቸው አካላት እንደሚላኩ ገልጸዋል።

ዩኒቨርሲቲው በነጻነት በራሱ መንገድ ተማሪዎችን መልምሎ በማስተማር የተሻሻለ አገልግሎት እንዲኖር እየሠራ ስለመሆኑ ተናግረዋል።

ዩኒቨርሲቲው የመንግሥት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ የማሻሻል ተልዕኮ ስላለው በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚታዩ ችግሮችን እንዴት መፍታት ይቻላል በሚለው በርካታ ጥናቶች አድርጓል። በብዛት ኢትዮጵያ ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ ከኢኮኖሚ ልማት፣ በተለያዩ ተቋማት በንግድና በኢንቨስትመንት አሠራር ላይ የተደረጉ ጥናቶች መሆናቸውን ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል።

የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥን በማዘመን አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል ያስፈልጋል ያሉት ፕሮፌሰር ፍቅሬ፤ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትን ለማስረጽ ዩኒቨርቲው የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ለተቋማት በማላመድ ለማስተላለፍ በመሥራት ላይ ነው ብለዋል።

በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ያሉ ሠራተኞች አስተሳሰብ ካልተቀየረ ለውጥ ሊመጣ አይችልም። በበርካታ ተቋማት የሚታዩ ችግሮች ከሠራተኛ አስተሳሰብ ጋር የሚያያዙ በመሆናቸው የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣና ቀልጣፋ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር በሥልጠና የመደገፍ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ወደ ራስ ገዝነት እንዲገቡ በትምህርት ሚኒስቴር አቅጣጫ ተቀምጧል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የሽግግር እቅድ አዘጋጅቶ ራስ ገዝ ለመሆን እየሠራ ነው። አሁን ላይ የመጀመሪያ ምዕራፍ ሥራዎች እየተሠሩ ሲሆን በ2020 ዓ.ም ሙሉ ለሙሉ ራስ ገዝ የመሆን እቅድን ይዞ እየሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

# በአትክልትና ፍራፍሬ እየመጡ ያሉ ለውጦችን አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- በአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ እየመጡ ያሉ ለውጦችን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባ የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር አምራችና ላኪዎች ማኅበር አስታወቀ።

የማህበሩ ዋና ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ ዘውዴ፤ በአበባ፣ በአትክልትና በፍራፍሬ ዘርፍ እየመጡ ያሉ ለውጦችን አጠናክሮ በማስቀጠል የውጭ ምንዛሬ እና የሥራ እድል ፈጠራውን ማሳደግ እንደሚገባ ለኢፕድ ገልጸዋል።

አሁን ያሉትን የአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ምርታማነትን በማየት የግብርና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ወደ ዘርፉ እየገቡ መሆኑን ጠቁመው፤ ለዘርፉ በተሰጠው ልዩ ትኩረት ችግሮችን መፍታት የሚያስችሉ አሠራሮች እየተዘረጉ ናቸው ብለዋል። አሠራሮቹም አርሶ አደሩን ከባለሀብቱ ጋር የሚያቀናጁና ለፓርኮች ሰፊ ግብዓት ማቅረብ እንዲቻል የሚያደርጉ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ቴዎድሮስ ገለጻ፤ መንግሥት ከዘርፉ የሚገኙ ምርቶችን እሴት ለመጨመር ከ25 ቢሊዮን ብር በላይ መድቦ የቡሬ፣ የቡልቡላ፣ የይርጋለምና ሌሎችንም የተቀናጁ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች አቋቁሟል። ፓርኮቹ በታሰበው ልክ ውጤታማ እንዲሆኑ የገበያ ትስስሮችን ማስፋት ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ ለሆርቲካልቸር ምርት በዓለም ላይ ምቹ ከሚባሉ ሶስት ሀገራት ተርታ እንደምትሰለፍ ያነሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ከዘር ጀምሮ በሀገር ውስጥ የማይመረቱ ግብዓቶች በመኖራቸው በሀገር ውስጥ የሚመረቱበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚገባ አመልክተዋል።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የአበባ፣ አትክልትና ፍራፍሬ ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ግማሽ ትሪሊዮን ዶላር ዓመታዊ ንግድ የሚካሄድበት ነው። ኢትዮጵያ በዘርፉ ካላት እምቅ አቅም አንጻር በቂ ገቢ እያገኘች ባለመሆኑ የተደራጀ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል።

በዘርፉ ላይ የሚታዩ የግብዓትና የተለያዩ ችግሮችን ለመፍታት በግብርና ሚኒስቴር በኩል የተጀመሩ ሥራዎች አበረታች መሆናቸውን የገለጹት አቶ ቴዎድሮስ፤ በዘርፉ ላይ እየተከናወነ ያለውን ስትራቴጂ በማጠናቀቅ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ጠቅሰዋል።

ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ ከምታቀርበው የሆርቲካልቸር ምርት ውስጥ ከ70 በመቶ በላይ ድርሻ የሚይዘው የአበባው ዘርፍ መሆኑን አመልክተው፤ የተቀረው የአትክልትና ፍራፍሬ ድርሻ እንደሆነ አቶ ቴዎድሮስ አስታውቀዋል።

እስራኤልና ኔዘርላንድ በዘርፉ ኢትዮጵያን የሚበልጧት ተቀናጅተው በመሥራታቸው ነው። ይህንን ተሞክሮ ወደ ሀገር ውስጥ በማምጣት የወጡ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ በማድረግ የበለጠ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ገልጸው፤ ለግብርና ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች በቂ ግበዓት ማቅረብና ለውጭ ገበያ እየቀረበ ያለውን የምርት መጠን ማሻሻል አስፈላጊ እንደሆነ አውስተዋል።

እየተሠሩ ያሉ ጅምር ሥራዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል የመሠረተ ልማትና መሻሻል ያለባቸው መሰል ችግሮችን መፍታት ከተቻለ ዘርፉ የውጭ ምንዛሬን ከማስገኘት ባሻገር የሥራ እድል ፈጠራውን ማሳደግ ላይ የሚኖረው ድርሻም ቀዳሚ እንደሚሆን ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።



# በመዲናዋ በአረንጓዴ ዐሻራ 17 ሚሊዮን ችግኞች ይተከላሉ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ በዘንድሮ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር በመጪው ክረምት 17 ሚሊዮን ችግኞች እንደሚተከሉ የአዲስ አበባ ከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ አደባባይ ሰንደቅ በተለይ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በሁለተኛው ምዕራፍ ሁለተኛ ዙር የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ሀገር በቀል ዛፎች፣ ለምግብነት፣ ለመድኃኒትነት የሚያገለግሉ የቅመማ ቅመሞች የተለያዩ ችግኞች በመዲናዋ ይተከላሉ።

በአዲስ አበባ ከተማ ደረጃ 17 ሚሊዮን ችግኞች በመጪው ክረምት ይተከላሉ ያሉት አቶ አደባባይ፤ ከዚህ ውስጥ 15 ሚሊዮን ችግኞች በቢሮው አቅም የተዘጋጁ ሲሆን፤ ቀሪው ሁለት ሚሊዮን በባለሀብቶች፣ በድርጅቶችና በማህበረሰቡ ንቁ ተሳትፎ እንደሚሸፈን ጠቁመዋል።

የከተማዋ የአረንጓዴ ልማት መርሃ ግብርን ለማስቀጠል በተለያዩ ችግኝ ጣቢያዎች ሀገር በቀልና የፍራፍሬ ችግኞችን የማፍላት ሥራ በመከናወን ላይ መሆኑን የገለጹት አቶ አደባባይ፤ በመጪው ክረምት የችግኝ ሥራዎችን ለመትከል የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በመጠናቀቅ ላይ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

አዲስ አበባን አረንጓዴ በማልበስ ለነዋሪዎቿ ምቹና ውብ ከተማ ለማድረግ ሁላችንም ችግኝ መትከል አለብን ያሉት አቶ አደባባይ፤ ችግኝ መትከል ብቻ ሳይሆን ተንከባክበን እንዲጸድቁና ፍሬ እንዲያፈሩ ማድረግ የሁሉም ኃላፊነት ነው ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ባለፉት ዓመታት በተከናወኑ የአርንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብሮች በርካታ የተራቆቱ አካባቢዎችን ማልማት እንደተቻለ ያነሱት አቶ አደባባይ፤ በአዲስ አበባ በተከናወኑ የአርንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ሁለት ነጥብ ስምንት ከመቶ የነበረውን የከተማዋን የአረንጓዴ ሽፋን ወደ 15 በመቶ ማሳደግ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

አዲስ አበባ ከተማን የአረንጓዴ ሽፋን ወደ 30 ከመቶ ለማድረስ እየተሠራ እንደሚገኝ የገለጹት አቶ አደባባይ፤ ህብረተሰቡ እንደዚህ ቀደሙ ሁሉ በተፈጥሮ ሀብትና ሥነ-ምህዳር ጥበቃ እያደረገ ያለውን ርብርብ በዘንድሮ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብርም አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ በዘንድሮ ዓመት አረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር ስድስት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል። የችግኝ ቁጥር በሄክታር ሲሰላ ዘንድሮ ተከላ የሚደረግበት አንድ ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት እንደሚሆን ግብርና ሚኒስቴር ገልጿል።

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሃሳብ አመንጪነት በተጀመረው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር እስካሁን ከ32 ነጥብ አምስት ቢሊዮን በላይ ችግኞች የተተከሉ ሲሆን በቀጣይ ሶስት ዓመታት ደግሞ 17 ነጥብ አምስት ቢሊዮን በመትከል 50 ቢሊዮን ችግኞችን በስምንት ዓመታት ውስጥ ለመትከል እቅድ ተይዟል። እስካሁን ለተተከሉት ችግኞች በተደረገው ክትትል እና እንክብካቤ የችግኞቹ የጽድቀት መጠን ከ90 በመቶ በላይ መድረሱም ተመላክቷል፡፡

# በአቪየሽን ሴኪዩሪቲ ዘርፍ የሪፎርም ሥራዎች ተጨባጭ ውጤቶች ተመዝግበዋል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**




አዲስ አበባ፡- በአቪየሽን ደህንነት (ሴኪዩሪቲ) ዘርፍ በተከናወኑ የሪፎርም ሥራዎች ተጨባጭ ውጤቶችን ማስመዝገብ መቻሉ ተገለጸ። ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ለምታስተናግደው ሀገራዊ የአቪዬሽን የደህንነት ኦዲት የማስጀመሪያ ሥነ-ሥርዓት ትናንት ተካሂዷል።

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተርና የሲቪል አቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ ሲሳይ ቶላ በወቅቱ እንደገለጹት፤ በአቬየሽን ሴኪዩሪቲ ዘርፍ በተከናወኑ የሪፎርም ሥራዎች የዘርፉን አደረጃጀታዊ መዋቅርና የአሠራር ሥርዓት ላይ ስር ነቀል ለውጥ በመደረጉ ተጨባጭ ውጤቶችን ማስመዝገብ ተችሏል።

አቬየሽኑ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ በተከናወኑ የሪፎርም ሥራዎች የአቬየሽን ሴኪዩሪቲ ዘርፍ ሥራ በአሠራር ሥርዓት እንዲዘምን፣ በሠለጠነ የሰው ኃይል እንዲጠናከር እንዲሁም ዘመኑን የዋጀ ቴክኖሎጂ እንዲታጠቅ መደረጉን ጠቅሰዋል።

አሜሪካው የትራንስፖርት ደህንነት አስተዳደር የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይ፣ የካናዳና እስራኤልን ጨምሮ ሌሎች 10 ዓለም አቀፍ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ኦዲቶችን ያለ ምንም ግኝት ማጠናቀቅ መቻሉ ለዚህ ማሳያ ነው ብለዋል። ኢትዮጵያ ከዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ተቋም ጋር አብሮ በመሥራት ረጅም ዓመታትን ማሳለፏንም ተናግረዋል።

በእስካሁን በተከናወኑ ተግባራት በኢትዮጵያ ጠንካራ የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ሥርዓት ተገንብቷል ያሉት አቶ ሲሳይ፤ በቀጣይም በአፍሪካ ምርጥ የአቪዬሽን ሴኩዩሪቲ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ለመሆን የተያዘውን ስትራቴጂክ ዕቅድ ለማሳካት የሚያስችል መሠረት መጣሉን ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ሲሳይ ገለጻ፤ በፈጣን እድገትና ተለዋዋጭ በሆነው የአቪዬሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ የሚከናወነው የአቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ሥራ ሁሌም ንቁ የሆነ አመራርና የሰው ኃይል በመያዝ ከዘመኑ ጋር ፈጥኖ በመገኘት በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል።

በተለይ በፈጣን የእድገት ጉዞ ላይ ያለውና በአማካኝ በዓመት ከ 10 ሚሊዮን በላይ መንገደኞችን እንዲሁም ከ700 ሺህ ቶን በላይ የካርጎ ጭነት የሚያጓጉዘው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ደህንነት ማረጋገጥ የመሥሪያ ቤቱ ቀዳሚ ተግባር ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የአቪዬሽን ደህንነት እንዲጠበቅ የብሔራዊ ሲቪል አቪዬሽን ሴኪዩሪቲ ኮሚቴ አቋቁማ እየሠራች ትገኛለች ያሉት አቶ ሲሳይ፤ ይህም የዓለም አቀፉ ሲቪል አቬየሽን ድርጅት አስገዳጅ መስፈርት በማሟላት የአቬየሽን ደህንነትን በአስተማማኝ መልኩ ለማረጋገጥ በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን አብራርተዋል።

አቶ ሲሳይ፤ ኢትዮጵያ የአቪዬሽን ዘርፍን ለማሳደግ በእኤአ 1944 በ52 ሀገራት መካከል የተፈረመውን የቺካጎ ስምምነት በመፈረም ከአፍሪካ ቀዳሚ ሀገር መሆኗን ጠቅሰው፤ ከዚያን ጊዜ አንስቶ ለዘርፉ ማደግ ከድርጅቱ ጋር በትብብር እየሠች ትገኛለች።

በዓለም አቀፉ የሲቪል አቪዬሽን ድርጅት በኦዲት ባለሙያዎች የሚካሄደው ይህ ኦዲት ከ 12 ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚካሄድ መሆኑ ታውቋል።

# ስውጭ ገበያ ከቀረበ የቡና ምርት አንድ ቢሊዮን ዶላር ገቢ ተገኘ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- ባለፉት 10 ወራት ለውጭ ገበያ ከቀረበ 210 ሺህ ቶን ቡና አንድ ቢሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ገለጸ። የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አዱኛ ደበላ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ለውጭ ገበያ የምታቀርበው የቡና ምርት በየዓመቱ እየጨመረ ነው።

በተያዘው በጀት ዓመት አሥር ወራትም 210 ሺህ ቶን ቡና ለውጭ ገበያ መቅረቡን ገልጸዋል። ይህም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ብልጫ እንዳለው ጠቁመው በዚህም 1 ቢሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱን ነው የጠቆሙት።

ኢትዮጵያ ከ50 እስከ 60 ለሚሆኑ ሀገራት ቡና የምትልክ መሆኑን ገልጸው የመዳረሻ ሀገራትን ቁጥር ለማስፋት እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

ለዚህም በተለያዩ ሀገራት የቡና አውደ ርዕዮችን በማዘጋጀትና ሌሎች ተግባራትን በማድረግ ቡናን የማስተዋወቅ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

ከቡና ንግድ ጋር በተያያዘ የሚስተዋሉ ሕገ-ወጥ ተግባራትን ለማስቀረትና የዘርፉን የውጭ ንግድ አፈጻጸም ለማሳደግ ዘመናዊ አሠራር ገቢራዊ መደረጉን ጠቁመዋል።

አሜሪካ፣ ጃፓን፣ ቤልጂየም፣ ጀርመንና ሳኡዲ አረቢያ የኢትዮጵያ ቡናን በብዛት ወደ ሀገራቸው የሚያስገቡና የሚጠቀሙ መሆናቸው መገለጹን ኢዜአ ዘግቧል ።

# በዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪና ተጽዕኖ ፈጣሪ ስታርት አፖችን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

በዘለለ በቴክኖሎጂ፣ በኢኖቬሽን እንዲሁም በፖለቲካ ጭምር መሪና ተጽዕኖ ፈጣሪ እንዲሆኑ እያስቻላቸው ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያም በስታርትአፕ እንቅስቃሴና ሥነ ምህዳር ልማት ዝቅተኛ መሆኗን መንግሥት ተረድቶ ዘርፉን ለማበረታት ከተለያዩ የልማት አጋሮች ጋር እየሠራ መሆኑን አስታውቀዋል።

ስታርትአፖች ለሀገር እድገት ሞተር በመሆናቸው መንግሥት በስታርትአፕ ሥነ ምህዳር ግንባታ ላይ ለውጥ የሚያመጡ ሥራዎችን እየሠራ በመሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስማችን ከፍ ማለት ችሏል ብለዋል፡፡

እንደ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ መንግሥት ለስታርትአፕ ሁለንተናዊ እድገት የፖሊሲ ርምጃዎችንና በተቋማት ቅንጅት የሚተገበሩ ኢኒሼቲቮችን ይፋ አድርጓል። በጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት የተካሄደው የብሔራዊ የስታርትአፕ ሁነት አንዱ ማሳያ መሆኑን ገልጸዋል።

በዚህ ሁነትም ከ300 በላይ ስታርትአፖች ሥራቸውን በኤግዚቢሽን መልክ አቅርበው ልምድና ልውውጥ ከመደረጉም ባለፈ ለስታርትአፖች ምቹ ምህዳር የሚፈጥሩ የተለያዩ የፖሊሲ ውሳኔዎች ይፋ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አመራር ሰጪነት ጥቅምት 2016 ከግሎባል ኢኖቬሽን ኢኒሼቲብ ጋር በመተባበር የአፍሪካ ስታትርትአፕ ሽልማትን ያዘጋጀች ሲሆን፤ ይህም ለሀገር በቀልና ለአፍሪካ ስታርትአፖች መበረታታት ዕድል እንደፈጠረ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የመላው አፍሪካ ስታርትአፕ ውድድርንና ሽልማትን ጥቅምት 2017ዓ.ም እንድታዘጋጅ መመረጧን ጠቅሰው፥ ይህም ሥራ ፈጠራንና ኢኖቬሽንን ለማበረታት እድል ይፈጥራል ሲሉ አስረድተዋል።

እኤአ በ2023ቱ አህጉር አቀፍ የስታርትአፕ ውድድር 731 የኢትዮጵያ ስታርትአፖች በውድድሩ ተሳትፈው 68ቱ አሸናፊ ሆነው የተለዩ ሲሆን፤ አሸናፊ ስታርትአፖቹ በ2024ቱ ዓለምአቀፉ የስታርትአፕ ውድድር ላይ እንደሚሳተፉ አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ክህሎት ለሀገር የወደፊት እጣ ፈንታ ወሳኝ በመሆኑ የኢትዮጵያ ልጆች በፈጠራ ሥራና በክህሎት ልቀው እንዲወጡ እናበረታታለን ብለዋል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚል በበኩላቸው የኢትዮጵያን ችግር በኢትዮጵያውያን ስታርትአፖች ለመፍታት እየተሠራ ነው ብለዋል።

ለኢኖቬሽንና ፈጠራ ስራዎች የተሰጠው ትኩረት ስታርትአፖች እንዲስፋፉ ምቹ እድል እየፈጠረ መሆኑን ገልጸው፤ በዚህም የማህበረሰቡን ችግር የሚፈቱ የፈጠራ ሥራዎችና ስታርትአፖች ወደ ገበያው እየተቀላቀሉ መሆኑንም አመልክተዋል።

ኢትዮጵያ መገንባት የምትፈልገውን ክህሎትና ፈጠራ መር ኢኮኖሚ እውን ለማድረግ ችግር ፈቺ የፈጠራ ሥራዎችን በስፋት መሥራት እንደሚገባ አስታውቀዋል።

# የፖለቲካ ፓርቲዎች በምክክሩ በመሳተፍ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ሀገራዊ ምክክር በየዓመቱ የሚደረግ ነገር አይደለም ያሉት አቶ ግርማ፤ በሂደቱ ተሳታፊ ያልሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምክክሩ በመሳተፍ ዐሻራቸውን ማኖር አለባቸው ብለዋል።


እንደ ኢዜማ በሀገራዊ ምክክሩ ስንሳተፍ ዋነኛው ዓላማችን ሀገር በዘላቂ መሠረት ላይ እንድትቆምና በማያግባቡን ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ከስምምነት እንድንደርስ በማሰብ ነው ያሉት አቶ ግርማ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች የፖሊሲ አጀንዳዎችን እና የሀገራዊ ምክክር አጀንዳዎችን ለይቶ ማየት እንደሚጠበቅባቸው ተናግረዋል።

እንደ አቶ ግርማ ገለጻ፤ እንደ ሀገር ሀገራዊ ምክክሩ መደረጉ ትልቅ ርምጃ ነው። አሁን ምክክሩ ባለበት የአጀንዳ አሰባሰብ ደረጃ በመወያየት አጀንዳ እየተለየ መሆኑን አመላክተው፤ በምን ጉዳይ ላይ እንደ ሕዝብ መወያየት እንዳለብን ማወቅ መቻላችን በራሱ ትልቅ ነገር ነው ብለዋል።

ታሪካዊ ኃላፊነት የተሰጠው ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኃላፊነቱን በሚገባ እንደሚወጣ እምነት እንዳላቸው የተናገሩት አቶ ግርማ፤ ኮሚሽኑ የተወሰኑ መንገዶችን ልንሻገርበት የምንችልበትን ሀዲድ መዘርጋት ከቻለ በራሱ ትልቅ ስኬት መሆኑን ጠቁመዋል።

ታዋቂ ግለሰቦች፣ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም የተለያዩ አካላት ተሰባስበው አገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ እየተወያዩ መሆኑ ትልቅ አጋጣሚ መሆኑን ተናግረው፤ የሀገራችን ችግሮች በውይይት መታወቁ መልካም ነው ብለዋል።

ሌላኛው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ሃሳባቸውን የሰጡት ተሳታፊ ሙሉጌታ ደበበ (ዶ/ር) ለ50 ዓመታት



**አቶ ግርማ ሰይፉ**

ገደማ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ተሳትፎ እንደነበራቸው ገልጸው፤ አሁን እንደ ሀገር ያሉትን ችግሮች ተቀምጦ መወያየት መቻል ያልተለመደ እና መልካም እድል መሆኑን ተናግረዋል።

በምክክሩ ዋና ዋና የሚባሉትን ችግሮች መፍታት ከተቻለ ቀሪዎቹ በጊዜ ሂደት ሊፈቱ ይችላሉ የሚሉት ሙሉጌታ (ዶ/ር)፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለችግሮች መፍትሄው መወያየት ብቻ መሆኑን በመረዳት በውይይቱ መሳተፍ አለበት ብለዋል።

ጦርነት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ተሞክሮ ለውጥ



**ሙሉጌታ ደበበ (ዶ/ር)**

አለማምጣቱን አስታውሰው ፤ያሉትን ችግሮች በጠብመንጃ ሳይሆን በጠረጴዛ ዙሪያ በውይይት መፍታት አለብን ብለዋል። ሁሉም ዜጋ በምክክሩ በመሳተፍ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ እንዳለበትም አክለታ ገልጸዋል።

ሕዝብ ጦርነት በቃን ብሎ ከሀገራዊ ምክክሩ ትልቅ ውጤት እየጠበቀ መሆኑን የጠቆሙት ሙሉጌታ (ዶ/ር)፤ እየተሳተፍኩበት ባለው የአዲስ አበባ የአጀንዳ ማሰባሰብ የምክክር ጉባዔ ምክክሩ በጥሩ ሁኔታ እተከናወነ በመሆኑ የሚጠበቀው ውጤት ይገኛል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ ብለዋል።

# ከበልግ እርሻ ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ማሳውን በበልግ ሰብል የመሸፈን ሥራ በንቃት እየሠራ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በአየር ንብረቱ ምቹነት የተነሳ በሰብል ለመሸፈን የታሰበውን ሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ወደ ሶስት ሚሊዮን 562 ሺህ 68 ሄክታር መሬት ከፍ እንዲል ተደርጓል ሲሉ አስታውቀዋል።

በዘር የሚሸፈነው የመሬት ስፋት በማደጉ ደግሞ ከታቀደውን 63 ሚሊዮን ኩንታል ምርት በላይ ምርት የሚገኝበትን አማራጭ ያሰፋዋል ብለዋል።

አቶ ከበደ እንዳስረዱት፤ በበልግ እርሻ ከእስከ ግንቦት 18 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ሶስት ሚሊዮን 562 ሺህ 68 ሄክታር መሬት ለዘር የማዘጋጀት ሥራ ተሠርቷል።

ከተዘጋጀውም መሬት ውስጥ ሶስት ሚሊዮን 501 ሺህ 173 ሄክታር መሬቱ በዘር መሸፈኑን አስታውቀዋል። ለበልግ እርሻ የምርጥ ዘር፣ የሜካናይዜሽንና የአፈር ማዳበሪያ ተደራሽ የማድረግ ሥራ በሰፊው እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

የምርትን ብክነት ለመቀነስ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በግብርናው ላይ ተግባራዊ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት አቶ ከበደ፤ ቴክኖሎጂን የመጠቀም ሥራ ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ ባለፈ የምርት ብክነትን ለመቀነስ ያግዛል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

በ2016 የበልግ እርሻ ለማግኘት የታቀደውን ምርት ለመሰብሰብ ከተገዛው 19 ነጥብ አራት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ውስጥ አብዛኛው ወደ ሀገር ውስጥ ገብቶ ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑን አንስተዋል።

ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የግብርና ባለሙያው፣ አመራሩ ከአርሶ አደሩ ጋር በቅርበት እየሠራ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

# ባንኩ የተበላሸ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ለመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴው ሪፖርት በትናትናው ዕለት አቅርቧል።

የባንኩን የዘጠኝ ወር አፈፃፀምና የአምስት ዓመት የሥራ ትግበራን ሪፖርት ተከታትለው የማጠቃለያ ንግግር ያደረጉት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ዋና ሰብሳቢ ፕሮፌሰር መሀመድ አብዱ እንደገለጹት፤ ባንኩ እየሠራው ያለው ሥራ የሚያበረታታ ቢሆንም አሁን ያለበትን ሰባት ነጥብ ስምንት በመቶ የተበላሸ ብድር ምጣኔን ዝቅ ለማድረግ በትኩረት መሥራት አለበት።

ባንኩ ልማታዊ ድርጅት እንደመሆኑ ለወጣቶች ተጠቃሚነትን ይበልጥ ለማሳደግ መሥራት አለበት ብለዋል። ባንኩ የሥራ አካባቢውን ምቹ በማድረግ ከሠራተኞችና ከማህበረሰቡ የሚነሱ ቅሬታዎችን አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት አሠራሩን በቴክኖሎጂ የማስደገፍ ሥራ መሥራት ይኖርበታል ሲሉ ጠቁመዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ዶክተር ስለሽ ኮሬ በበኩላቸው ፤ ባንኩ ያለበትን ሰባት ነጥብ ስምንት በመቶ የተበላሸ ብድር ምጣኔ ዝቅ ለማድረግ በትኩረት መሥራት ይኖርበታል።

ባንኩ ከአምስት ዓመት በፊት የነበረበትን ከ57 በመቶ በላይ የተበላሸ ብድር ምጣኔ ለመቀነስ የሠራው የተለያየ የለውጥ ሥራ የሚበረታታ መሆኑን ገልጸው፤ የሠራው የለውጥ ሥራ የነበረበትን ከ57 በመቶ በላይ የተበላሸ የብድር ምጣኔ ወደ ሰባት ነጥብ ስምንት በመቶ ዝቅ እንዲል አድርጎታል ብለዋል።

ባንኩ የብድር አቅርቦትን በማሳደግ ሰፊ እድል መፍጠር አለበት ያሉት ምክትል ሰብሳቢው፤ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት እንዲችል አሁን ያለበትን ሰባት ነጥብ ስምንት በመቶ የተበላሸ የብድር ምጣኔ ዝቅ ለማድረግ መሥራት ይኖርበታል ሲሉ ገልጸዋል።

ባንኩ ያለበትን የተበላሸ የብድር ጫና ለመቀነስ እየተከተለ ያለው የአሠራር ሂደት ጥሩና የሚበረታታ ነው ያሉት ዶክተር ስለሽ፤ አሁን ያለበትን የተበላሸ ብድር ምጣኔ ዝቅ ማድረግ ይኖርበታል ብለዋል።

ባንኩ የትርፍ ገቢውን ለማሳደግ የተለያዩ አማራጮችን መጠቀም ይጠበቅበታል፤ ገቢው በማሳደግ የብድር አገልግሎቱን ማስፋት እንዳለበት ገልጸዋል። የአበደረውን ብድር ፕሮግራም በማውጣት መሰብሰብ አለበት ያሉት ምክትል ሰብሳቢው፤ ያበደረውን ብድር በፕሮግራም መሰብሰቡ አሁን ያለበትን የተበላሸ የብድር ምጣኔ ዝቅ ለማድረግ ያግዘዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ባንኩ በተያዘው በጀት ዓመት ዝቅተኛ አፈፃፀም ያሳየባቸው የተለያዩ ዘርፎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ እንዲሠራ አመላክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከችግሮቻችን የምንወጣበት ተጨባጭ አማራጭ!

እኛ ኢትዮጵያውያን የረጅም ዘመናት የሀገረ መንግሥት ታሪክ ባለቤቶች ነን። በነዚህ ዘመናትም እንደ አንድ ትልቅ ሕዝብ ብዙ አሉታዊ እና አወንታዊ ክስተቶችን አሳልፈናል። ከፍ ካለ ሥልጣኔ ጀምሮ ልብን የሚሰብሩ የግጭት እና የጦርነት ፤ የረሀብ እና የጉስቁልና ታሪኮችን ለማለፍ ተገድደናል።

በአንድ ወቅት የአክሱም ሐውልቶችን ፤ የላሊበላ ቤተመቅደስን ...ወዘተ መገንባት የቻልነውን ያህል ፤ ይህንን ድንቅ የሰው ልጅ የአዕምሮ እሳቤ እና የእጅ ጥበብ ባለመደማመጥ መርገምት ማስቀጠል አቅቶን የትናንት ገናናነታችን ነበር በሚል የታሪክ ትርክት ዘመን እንዲያስቆጥር አድርገናል ።

ሁሉን አጥፍቶ / አፍርሶ በአዲስ በመተካት ላይ የተመሰረተው ሀገራዊ የለውጥ መነሳሳታችን ፤ ተተኪ ትውልዶች ትናንታቸውን በተጨባጭ አውቀው ፤ ትናንትን መሠረት ያደረገ ጅማሪ እንዳይኖራቸው ተግዳሮት ሆኖባቸዋል ፤ ስለ ትናንት በቂ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው በማድረግ ዛሬያቸው በብዙ ግራ መጋባት እንዲፈተን አድርጎታል ።

ከዚህም ባለፈ በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶች የታሪክ ክፍተት በፈጠራቸው የተዛቡ ትርክቶች ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍሉ ሆነዋል። ይህም አጠቃላይ በሆነው የትውልድ ቅብብሎሽ የሚጠበቀውን እንደ ሀገር የመለወጥ ፣ የማደግ እና ከትናንት የተሻለ ማኅበረሰብ እና ሀገር የመገንባት መሻት እውን ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል።

በኢትዮጵያ በተለያዩ ወቅቶች የተለያየ ስም የተሰጣቸው ጦርነቶች እና አብዮቶች ተካሂደዋል። እነዚህ ጦርነቶች እና አብዮቶች እንደ ሀገር የጠበቅናቸውን እና ተስፋ ያደርግናቸውን ማኅበረሰባዊ መሻታችንን ተጨባጭ ሊያደርጉልን አልቻሉም ። ለአንዳንድ ችግሮቻችን መፍትሄ ይዘው የመጡ ቢመስልም ከዚህ በተቃራኒው ሄደው ለተጨማሪ ሀገራዊ ፈተናዎችን ዳርገውናል።

እንደ ሀገር ባለፉት ስድስት አስርት ዓመታት የሆነውን ብናነሳ እንኳን "ያለምንም ደም እንከኗ ይውደም፣ በጸና መንፈስ ኢትዮጵያ ትቅደም" በሚል ሀገራዊ የለውጥ መነሳሳት የተጀመረው አብዮት ፣ የቱን ያህል ዋጋ እንዳስከፈለንና እንደሀገር ምን እንዳሳጣን የአደባባይ ሚስጥር ነው ። አብዮቱ በማኅበረሰባችን ውስጥ ጥሎት ያለፈው ጠበሳም የቱን ያህል ከባድ እንደነበር ሁሌም የሚታወስ ነው።

ይህንን ሀገራዊ እውነታ በመቀልበስ በሚል በየመንደሩ የተጀመሩ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ከፍ ወዳለ የፖለቲካ ፍላጎቶች አድገው ፣ ብዙ ጠብመንጃ ያነገቡ ቡድኖችን በመፍጠር ወደ ለየለት የርስ በርስ ጦርነት ከቶናል። በዚህም ያሳለፍናቸው አስርት ዓመታት የቅርብ ትዝታዎቻችን ናቸው። እንደ ሀገር በሕዝባችን ውስጥ የፈጠሩትም የልብ ስብራት ቀላል አይደለም ።

አብዮቶቹም ሆኑ ጦርነቶቹ ፣ የአሸናፊ እና ተሸናፊ ትርክቶችን መሠረት ያደረገ የኃይል አስተሳሰብን የተደገፉ መሆናቸው ፣ ዘላቂ ሀገራዊ ሰላም ሆነ የጋራ ማኅበራዊ ፍላጎታችንን ተጨባጭ ለማድረግ አላገዙንም ። ከዚያ ይልቅ የእብሪት መንፈስን በመፍጠር ባልተገቡ የፖለቲካ ሴራዎች እንድንፈተን አድርገውናል ።

በአንድ በኩል በኃይል አሸናፊነቱን ያጸናው ቡድን አሸናፊነቱን ለማስቀጠል የኃይል እና የሴራ ፖለቲካን ዋንኛ አማራጭ አድርጎ መውሰዱ ፣ በሌላ በኩል ይህ የአሸናፊው የኃይል እና የሴራ እንቅስቃሴ እንደሀገር የሚፈጥረው ማኅበራዊ አለመረጋጋት በራሱ ሀገር ወደ ስክነት እና መረጋጋት እንዳትመጣ አድርጓታል።

ይህ በመሠረታዊነት ፍላጎቶችን በኃይል እና በሴራ በሌሎች ላይ በመጫን የመጣንበት ርቀት እንደሀገር የድህነት እና ኋላቀርነት ማሳያ የሆነች ኢትዮጵያን ፈጥሯል ። እውነታውን ተረድተን ፈጥነን መንቀሳቀስ ካልቻልን ችግሩ ድንገትም በብዙ መስዋዕትነት ዛሬ ላይ የደረሰችውን ሀገራችንን ሊያሳጣን እንደሚችል ለመገመት አይከብድም።

ለዚህ ደግሞ አሁን ላይ ያለን አማራጭ በልዩነቶቻችን /በፍላጎቶቻችን ዙሪያ በሰከነ መንፈስ ፣ በተረጋጋ አእምሮ ፣ የሀገር እና የትውልድ ኃላፊነት በሚሰማው ማንነት ቁጭ ብለን መነጋገርና መወያየት ይኖርብናል ፤ ከዚህ ቀደም ዓይናችንን ከፍተን ለማየት ያልቻልነውን ይህን አማራጭ ፈጥኖ መጠቀም ፣ ለዚህ የሚሆን ሁለንተናዊ ዝግጁነት መፍጠርም ይጠበቅብናል ። ለዚህ ደግሞ ከፊታችን ያለው ሀገራዊ ምክክር ትልቅ ዕድል ፣ በዕድል ውስጥ ያለ ተስፋችን ነው ።

ይህ ከችግሮቻችን የሚያወጣን ተጨባጭ አማራጭ ሁላችንንም ስለ ሀገራችን እና ስለ ሀገራዊ ተስፋችን ሁላችንንም በእኩል አሸናፊም/ ተሸናፊ የሚያደርገን ነው። ከዚህ ባለፈም እንደ ሀገር ተፈጥሮ ለማየት ለምንመኘው አዲስ የፖለቲካ ባህል ግንባታ ትልቅ አቅም ተደርጎ የሚወሰድ፣ ለቀጣይ ትውልዶችም የበለጸገች ሀገር ለመፍጠር መሠረት የሚሆን ነው።

ለዚህ ነው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ዶ/ር ሰሞኑን ፣ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት " ጦርነትና አብዮት የተሟላ መፍትሔ የማያመጡት አሸናፊ እና ተሸናፊ ስለሚያስከትሉ ነው። ቢዘገይም የተሸነፈው ለማሸነፍ ይታገላል። ያሸነፈውም ድሉን ለመጠበቅ ይዋጋል። ምክክር ግን ሁሉንም አሸናፊ ያደርጋል። ከተሸነፍንም ሁላችንም ለሀገራችን ብለን እንሸነፍ"

"ጦርነትን ኖረንበታል። የተወሰኑ ችግሮቻችንን ፈትተንበታል። አብዮትን ደጋግመነዋል። የተወሰኑ ችግሮችን ፈትተንበታል ፤ በሁለቱም ያልተፈቱትን ችግሮች ለመፍታት የቀረን መንገድ ምክክር ነው ማለታቸው። ለምክክሩ ስኬታማነት ሁሉም ዜጋ በሃላፊነት እንዲንቀሳቀስ ሲሉ ጥሪ ማቅረባቸው!

**አዲስ ዘመን**
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ
ኢፕድ

**<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ</u>**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**<u>ዋና አዘጋጅ</u>**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**<u>አድራሻ</u>**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**<u>የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ</u>**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**<u>የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር</u>**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**<u>የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ</u>**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**<u>የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች</u>**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**<u>የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል</u>**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**<u>የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ</u>**
ስልክ - 011-1-26-43-39

<u>ማከፋፈያ</u> ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዜጎችን ከሀሰተኛ መረጃዎች ለመታደግ

ቦጋለ አበበ

ሰሞኑን የአዲስ አበባ ፖሊስ በዩ ቲዩብ እና ቲክቶክ ከሕዝብ ባህል እና ሞራል ውጭ የሆነ ሀሰተኛ የፈጠራ ታሪኮችን እንደ እውነተኛ ታሪክ እያደረጉ ሲያቀርቡ አገኘኋቸው ያላቸውን ሰዎች በቁጥጥር ስር አውሏል፡፡ እነዚህ ወጣቶች ቢሮ ተከራይተው፣ ካሜራ ገዝተው፣ ስክሪፕት አርቅቀው፣ ቃለመጠይቅ ተለማምደው ነው ይህን የሚሠሩት፡፡ ይህ የሚያሳየን ብዙ ነገር አለ፡፡

በዋነኝነት ይህ የሚያሳየው የርዕይ መንጠፍ ወይም በተለምዶ ፈረንጆቹ «ፌለር ኦፍ ኢማጂኔሽን» የሚሉት ነው፡፡ በሲኒማው ዘርፍ ብዙ ርቀት የተጓዙት ሀገራት የፊልም ኢንዱስትሪውን የሚጠቀሙበት በእውነተኛው ዓለም የሌለ ነገር ግን ቢኖር ብለው የሚያስቡትን ነገር ለማሳየት ነው፡፡ ለዚያም ነው በእውነተኛው ዓለም የሌሉ ነገሮችን በፊልም የምናያቸው፡፡ ስናያቸው "ይሄማ ውሸት ነው፣ ይሄ ተጋነነ፣ ይሄ የማይመስል ነገር ነው" እንላለን፡፡ ያልናቸው ነገሮች ግን ብዙውን ጊዜ ዘግይቶም ቢሆን የቴክኖሎጂ ሰዎች እውን ሲያረጓቸው እናያለን፡፡

ሞባይል ስልክን ዛሬ ሁላችንም ከመያዛችን በፊት መጀመሪያ ላይ የፊልም ሃሳብ ነበር፡፡ አሁን ዓለምን ካጥለቀለቀው ሰው ሠራሽ አስተውሎት (አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ) አንስቶ አብዛኞቹ ዘመን ወለድ ቴክኖሎጂዎች በአንድ ወቅት የልብወለድ እና የፊልም ሃሳብ ነበሩ፡፡ ዛሬስ እኛ የምንሠራቸው የዩቲዩብ እና ቲክቶክ ቪዲዮዎች ወደፊት ምን አይነት ኢንዱስትሪን ይፈጥሩ ይሆን? ምን አይነት ቴክኖሎጂንስ ያዋልዱ ይሆን? አሁን በሚሠሩት ይዘት መሠረት ከሆነ ቀጥሎ የሚመጣው ውጤት ጥሩ እንደማይሆን ግልጽ ነው፡፡ እስኪ አስቡት ሰዎች ስራዬ ብለው እስኪርቢቶ ይዘው ወረቀት ገልጠው የሚጽፉት የፊልም ሃሳብ "ለባእድ አምልኮ መስዋእት ሊያደርጉ ልጃቸውን ስላረዱ ቤተሰቦች" "ስለ ግብረ ሰዶም" "በዘመዷ ስለተደፈረች ታዳጊ" እና መሰል አይነት ይዘቶች ነው፡፡ ያሳፍራል፡፡ ጭንቅላታችንን ጨምቀን የምናፈልቀው ሃሳብ ይህ ከሆነ ጭንቅላታችን ነጥፏል ማለት ነው፡፡

> **ሞባይል ስልክን ዛሬ ሁላችንም ከመያዛችን በፊት መጀመሪያ ላይ የፊልም ሃሳብ ነበር:: አሁን ዓለምን ካጥለቀለቀው ሰው ሠራሽ አስተውሎት (አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ) አንስቶ አብዛኞቹ ዘመን ወለድ ቴክኖሎጂዎች በአንድ ወቅት የልብወለድ እና የፊልም ሃሳብ ነበሩ**

ይህ ዛሬ ለዩቲዩብ ገበያ ተብሎ የሚፈበረክ ልብ ወለድ ነገ ይለመድና ሕዝባዊ ባህል ይሆናል፡፡ ሌሎች በፊልማቸው ያዩትን ቴክኖሎጂ በሳይንስ እውን ሲያደርጉት እኛ ደግሞ በፊልማችን የምናሳየው መላሸቅ በቀጣይ በሕይወታችንም ላይ ይተገበራል ማለት ነው፡፡

እርግጥ አንዳንድ ምሁራን እንደሚሉት ይህ ችግር የርዕይ መንጠፍ ችግር ሳይሆን ርዕያችን ዝና እና ገንዘብን ማዕከል ያደረገ መሆኑ ነው ይላሉ፡፡ ለምሳሌ በቅርቡ በማህበራዊ ሚዲያ ቁጣ ቀስቅሶ የነበረ አንድ አስነዋሪ የዩቲዩብ ትወና ላይ ተሳታፊ የነበሩ አንዲት ሴት እና አንድ ታዳጊ ህጻን ይቅርታ በጠየቁበት ሌላ ቪዲዮ ላይ እንደተናገሩት ከሆነ ወደዚህ አይነት ተሳትፎ የገቡበት ምክንያት 'ታዋቂ ለመሆን' በማሰብ ነው፡፡ በእርግጥም በተሳሳተ መንገድም ቢሆን ታዋቂ ሆነውበታል፡፡ እነሱን ከጀርባ ሆነው የሚያሠሩት ሰዎች ደግሞ ቪዲዮው ብዙ ጊዜ በመታየቱ ገንዘብ አትርፈውበታል፡፡ ስለዚህም ዓላማቸው ተሳክቷል ማለት ይቻላል፡፡ ያለንበት የኢኮኖሚ ችግር ሰዎች ማንኛውንም ነገር እንዲያደርጉ በር የሚከፍት ሊሆን ይችላል፡፡ ዝናውም ቢሆን የሚፈለገው ገንዘብ አስከትሎ ስለሚያመጣ ነው፡፡ ስለዚህም ሃሳባቸውን እንረዳለን፡፡ ነገር ግን ካልጠፋ ሃሳብ እንዲህ አይነት ሰንካላ ሃሳቦችን አዕምሮአቸው እንዴት አመነጨላቸው? የሚለው ሃሳብ ነው የሚያስጨንቀው፡፡

እርግጥ እንዲህ አይነት ነገር በኛ ሀገር ብቻ ያለ አይደለም፡፡ ባደጉትም ሀገራት እንዲህ አይነት የላሸቁ ሃሳቦች አሉ፡፡ ነገር ግን እንዲህ አይነት ሰዎች የሚስተናገዱበት ሥርዓትም አለ፡፡ በምንም መንገድ ግን ዋነኛ የትኩረት መስህብ እንዲሆኑ አይፈለግም፡፡ ለምሳሌ ከላይ እንደጠቀስናቸው አይነት ከባህል እና ወግ ያፈነገጡ ሃሳቦችን የሚያስተናግዱት የወሲብ ቻናሎች ሲሆኑ መንግሥታትም እነዚህ ቻናሎች እና ድርጅቶች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ያደርጋሉ፡፡ በተቃራኒው ለሀገር እና ለሕዝብ ፋይዳ አላቸው በሚባሉ እና ሀገራዊ ርዕይ (national vision) በሚሰበክባቸው የፊልም እና የሚዲያ መስመሮች ላይ ከፍተኛ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ለዚያ ነው አሜሪካ እና አውሮፓ የራሳቸውን ራዕይ እና እሴት የሚሰብኩበት የሆሊውድ ስቱዲዮዎች ላይ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት የሚያፈስሱት፡፡ እኛ ጋ ሁለቱም ቀስ በቀስ እየተደባለቁ ነው፡፡ እንዲያውም ይሄ ብዙ ኢንቨስትመንት የማይፈልገው እና ቁጥጥር የማይሻው የዩቲዩብ እና ቲክቶክ ዘርፍ ዋናውን የሲኒማ እና የሚዲያ ኢንዱስትሪ እየተጋፋና እያዳከመው ነው፡፡ ስለዚህም በቅርብ ጊዜ ዩቲዩቡ እና ቲክቶኩ ደካማ እና የላሸቀ ሃሳብ ካላቸው ባለቤቶች ጋር ሆነው ዋነኛ ሚዲያ (mainstream media) ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህም ዜጎችን ከሀሰተኛ መረጃዎች ለመታደግ እንዲሁም የማህበረሰብን ባህልና ወግ ከሚሸረሽሩ ከውሸት ታሪኮች መጠበቅ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ በዚህ እኩይ ተግባር ላይ ተሰማርተው የሚገኙ አካላትን እርማት መስጠት ካስፈለገን ከአሁኑ ነው፡፡ ከአሁኑ በማህበራዊ ሚዲያው ላይ የሚታዩ የአስተሳሰብ ውድቀቶችን በጠንካራ ሂስ ማረም እልፍ ካለም በሕግ አግባብ መቆጣጠር የግድ የሚሆነውም ለዚህ ነው፡፡ አልያም ዛሬ በእንቁላሉ ጊዜ በቸልታ ያለፍነው ውድቀት ነገ በበሬው ጊዜ ለማረም ያስቸግራልና ይታሰብበት፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የኢትዮጵያና የሶማሊላንድ ግንኙነት ቀጣናዊ ፋይዳ

እስማኤል አረቦ

179ሺ 119 ስኴር ኪሎ ሜትር ስፋት አላት:: የሕዝብ ብዛቷም 4ነጥብ 3 ሚሊዮን የሚጠጋ ነው። በመቶ ማይልስ ርዝምት ከገልፍ ኦ ኤደን ጋር ጠረፍ ትጋራለች:: በስተደቡብ ከኢትዮጵያ ጋር በስተምዕራብ ደግሞ ከጅቡቲ ጋር ትዋሰናለች:: በስተምስራቅ ደግሞ ከፊል ነጻነቷን ካወጀችው ከፑንትላንድ ጋር ትጎራበታለች:: ሶማሊላንድ::

ዋናዋ ሶማሊ ሪፐብሊክ በጣሊያን ቅኝ ግዛት ውስጥ የቆየች ስትሆን፤ ሶማሊ ላንድ በበኩሏ የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሆና እስከ 1960 ድረስ ዘልቃለች:: ሁለቱም ከቅኝ ግዛት ከወጡ በኋላ ውህደት ለመፈጸም ጥረት የተደረገ ቢሆንም ይህነኑ አካሄድ ሶማሊላንድ ስትቃወም ቆይታለች::

በተለይም የዚያድ ባሬ አስተዳደር ከመጣ በኋላ ይህንኑ በጉልበት የመዋሃድ እንቅስቃሴ በመቃወም ሰፊ ንቅናቄ ተደርጓል:: ይህን ተከትሎም ወደ እርስ በእርስ ጦርነት በመግባት በሁለቱም ወገኖች ላይ በርካታ ቁሳዊና ሰብዓዊ ኪሳራ ደርሷል:: በወቅቱም አምባገነኑ የዚያድ ባሬ መንግስትም በ10ሺዎች የሚቆጠሩ የሶማሊላንድ ተቃዋሚዎችን ገድሏል::

ሶማሊላንድ እኤአ ከ1991 ጀምሮ ነጻነቷን ያወጀችና ላለፉት 33 ዓመታትም እራሷን በራሷ ስታስተዳድር ቆይታለች:: የራሷ የሆነ መከላከያ ኃይል፤ መገበያያ ገንዘብና የውጭ ሀገራት የመጓጓዣ ሰነድ ያላት ነች:: ከዓለም ሀገራት ዕውቅና ባታገኝም በርካታ ሀገራት ግን ነጻ ሀገር ትታሰባለች::

ዓለም አቀፍ ተቋማትና ሀገራት ጭምር በየጊዜው በምታደርገው ምርጫ ላይ በመገኘት በታዛቢነት ሲገኙ ቆይተዋል:: ካላት ሰላምና አካባቢያዊ አቀማመጥ አኳያ የውጭ ባለሃብቶችን ቀልብ ትስባለች:: በርካታ ባለሃብቶችም በዚህች ሀገር ላይ መዋዕለነዋያቸውን ለማፍሰስ ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው::

በወደብ ልማትና ተያያዥ ዘርፎች አንቱታን ያተረፈው የተባበሩት ኢምሬትስ ንብረት የሆነው ዲፒ ወርልድ የበርበራ ወደብን ለማልማት ፍላጎት ማሳደሩና ወደ ስራ መግባቱ ለሶማሊላንድ ትልቅ ተስፋን ፈንጥቋል:: የዲፒወርልድ ውሳኔም በፋይናንስ እጥረት ለምትሰቃየው ሶማሊላንድም ከፍተኛ እፎይታ አስገኝቷል::

ይህንኑ ተከትሎ ኢትዮጵያም በበርበራ ወደብ ላይ የባለቤትነት መብት ወስዳ ወደ ልማት መግባቷ በአካባቢው መነቃቃትን ፈጥሯል:: የበርበራ ወደብን የኢምሬትስ መንግስት 51በመቶ፤ የሶማሊላንድ አስተዳደር 30 በመቶ እና የኢትዮጵያ መንግስት 19 በመቶውን በመውሰድ ወደቡን በጋራ በማልማት ላይ ይገኛሉ:: ይህም በሶማሊላንዶች በኩል እንደትልቅ ተስፋ የሚወሰድ ነው::

ሶማሊላንድ ነጻነቷን ካወጀች በኋላ ተደጋጋሚ ምርጫዎችን አካሂዳለች:: ምርጫዎቹ በዓለም አቀፍ መመዘኛዎች ጭምር በዲሞክራሲዊነታቸውና በሰላማዊነታቸው የተመሰከረላቸው ናቸው:: ለአብነትም እኤአ በ2003 እና በ2010 በሶማሊላንድ የተደረገው ምርጫ ሰላማዊ ከመሆኑም በላይ ገዢው ፓርቲ ለተቃዋሚ ፓርቲ ያለምንም ኮሽታ ስልጣኑን ያስረከበበትና በሰላማዊነቱም በአፍሪካ ተጠቃሽ ምርጫ ነው::

በ2107 በተደረገው ምርጫም የአውሮፓ ሕብረት፤ እንግሊዝ፤ ፈረንሳይ፤ አሜሪካ ሉኡኮቻቸውን በመላክ የምርጫውን ዴሞክራሲያዊነትና ሰላማዊነት ታዝበው ተመልሰዋል:: ስለምርጫው ዴሞክራሲያዊነትና ሰላማዊነትም ዕውቅና ሰጥተዋል::

ሶማሊላንድ ለምስራቅ አፍሪካ ቀጠና ወሳኝ ስፍራ ናት:: በገልአፍኤደን ዳርቻ የምትገኝ እና 1/3ኛው የሚሆኑ መርከቦች የሚጓጓዙበት የባቤል መንደብ መዳረሻ ናት:: ሶማሊለንድ ያለችበት አካባቢ በዓለም ላይ ያሉ ኃያላን ሀገራት የሚራኮቱበት ከፍተኛ የስህበት ማዕከል ነው::

በአሁኑ ወቀት አሜሪካ፤ ፈረንሳይ፤ ቻይና፤ ሩስያ፤ የተባበሩት አረብ ኢምሬት፤ ጣሊያን፤ ጃፓን የመሳሰሉ ሀገራት የጦር ሰፈር መስርተው የበላይነታቸውን ለማረጋገጥ ትንቅንቅ ውስጥ የገቡበት አካባቢ ነው:: በዚሁ አካባቢ ጅቡቲ ወሳኙን ድርሻ የያዘች ቢሆንም በቀጣይ ሶማሊላንድ የማይናቅ ድርሻ እንደሚኖራት ይገመታል::

**ኢትዮጵያና ሶማሊላንድ ያደረጉት ስምምነት ለኢትዮጵያም ጥቅሙ የጎላ ነው:: ኢትዮጵያ ከ33 ዓመታት በኋላ የባሕር በር የምታገኝበት አማራጭ የሚያሰፋ መግባቢያ ሰነድ (Memorandum of understanding) በኢትዮጵያ እና በሶማሊላንድ መካከል ከተፈረመ በኋላ በኢትዮጵያውያን ዘንድ አዲስ ተስፋ ፈንጥቋል**

ኢትዮጵያ ከሶማሊላንድ ጋር የቀረበ ግንነት አላት:: በ2004 ዓ.ም አካባቢ አገናኝ ጽህፈት ቤት ከፍታ ግንኙነቷን ከማጠናከር ባሻገር በኢትዮጵያ እና በሶማሊላንድ ያሉ የሶማሊ ተወላጆች ያላቸውን የሃይማኖትና የባህል አንድነት እንዲጠናከር ስትሰራ ቆይታለች:: ካለፈው ታህሳስ ወር ጀምሮ ደግሞ ግንኙነቱ ወዳ ላቀ ደረጃ ተሸጋግሯል::

ከሶማሊላንድ ጋር በተፈጸመው መግባቢያ ሰነድ ኢትዮጵያ ከ33 ዓመታት በኋላ የባህር በር የምታገኝበት አማራጭ ተገኝቷል:: ይህ የመግባቢያ ሰነድ ሲተገበር አካባቢያዊ መረጋጋት የሚያመጣና ኢትዮጵያም በቀጣናው ላይ አለኝ የምትለውን የባለቤትነት ጥያቄ መልስ እንዲገኝ በር የሚከፍት ነው:: ቀጠናዊ ሰላምን በማስፈን የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የተረጋጋ እንዲሆን የሚያስችል እንደሆነ ይታመናል::

ለሶማሊላንድም ቢሆን ትሩፋቱ የበዛ ነው:: በዓለም ላይ ካሉት 18 ድሃ ሀገራት ተርታ የምትቆጠረው ሶማሊላንድ ከኢትዮጵያ የወድብና የባህር በር ጥያቄ መቀበሏ ዝቅተኛ የሆነውን ኢኮኖሚዋን ለመደገፍና ከፍተኛ የሆነውን የስራ አጥ ቁጥር ለመቀነስ ዕድል ይሰጣታል:: ዓመታዊ ጥቅል ገቢዋ ከ2ቢሊዮን ዶላር ላልዘዘለው ለዚቹ ሀገር ከኢትዮጵያ ጋር የፈጠረችው ግንኙነት ከፍተኛ የኢኮኖሚ አቅምን የሚፈጥር ነው::

በኢትዮጵያና በሶማሊላንድ መካከል የተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ በሁለቱም ሕዝቦች ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነትን አግኝቷል:: የኢትዮጵያ ሔራልድ ጋዜጠኛ በሶማሊላንድ ዋና ከተማ ሀርጌሳ ተገኝቶ እንዳረጋገጠው ኢትዮጵያ እና ሶማሊላንድ ያደረጉትን ስምምነት ሕዝቡ በከፍተኛ ደስታ ነው የተቀበለው::

ሶማሊላንድ ነጻነቷን ያወጀችበትን ዕለት በማስመልከት አደባባይ የተገኙ የሀርጌሳ ነዋሪዎች እንደተናገሩት የተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ ሁለቱን ሀገራት የሚጠቅምና ግንኙነታቸውንም የሚጠናከር ነው:: ይህንን የመግባቢያ ሰነድ የሚቃወሙ አካላትም የኢትዮጵያ እና የሶማሊላንድን ግንኙነት የማይሹና የጋራ ዕድገትን የማይመኙ ናቸው ሲሉም ተደምጠዋል:: እነዚህን አካላት ወደ ጎን በመተው የተጀመረው ስምምነት ወደ መሬት እንዲወርድ አበክረው መስራት እንዳለባቸውም ተናግረዋል::

ዋዳኒ ናሽናል ፓርቲ የተሰኘውም የሶማሊላንድ ዋነኛ ተቃዋሚ ፓርቲ የተደረሰውን ስምምነት በአድናቆት ነው የተመለከተው:: የፓርቲው የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ መሀመድ ጂማ አዳም እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ከሶማሊላንድ ጋር ስምምነት ላይ መድረሷ ሁለቱንም ተጠቃሚ ያደርጋል:: ኢትዮጵያም የባሕር በር እና ወደብ ተጠቃሚ እንድትሆን ዕድሉን ይሰጣል፤ ለሶማሊላንድም ዘርፈ ብዙ ዕድሎችን ይዞ ይመጣል::

የሶማሊላንድ የኢንቨስትመንት ሚኒስትር አብዱረዛቅ ኢብራሂም በበኩላቸው እንደገለጹት በኢትዮጵያና በሶማሊላንድ መካከል የተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ ሁለቱንም ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው:: ሶማሊላንድ በባሕር የተከከበች ከመሆኗ አንጻር የኢትዮጵያ ባለሃብቶች በአሳ ልማትና ተያያዥ ዘርፎች እንዲሰማሩ ጥሪ አድርገዋል::

በተለይም ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ ያስመዘገበችውን ውጤት የኢትዮጵያ ባለሃብቶች በሶማሊላንድ እንዲደግሙት ፍላጎቱ እንዳላቸው ተናግረዋል:: ኢትዮጵያ ለዘመናት ተቆጣጥራ ከኖረችው የቀይባሕር አካባቢ በበርካታ ሴራዎች ምክንያት ከአካባቢው ገለል እንድትል ተደርጋለች:: በዚህም ዝናና ክብሯ ዝቅ ብሎ ተሰሚነቷ አሽቆልቁሏል:: የኢትዮጵያዊነት ስነልቦናም ክፉኛ ተጎድቶ ኖሯል::

የኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆንም ከስነልቦናዊ ቀውስ ባሻገር ለበርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ጫና ሕዝቡ እንዲጋለጥ አድርጎታል:: የኢትዮጵያን ክብርና ዝና ዝቅ እንዲል ከማድረጉም ባሻገር በኢኮኖሚ ረገድም ተጎጂ እንድትሆን አድርጓታል::

ለበርካታ መሰረተ ልማቶችና ለድህነት መቀነሻ ልማቶችን ይውል የነበረውን ከ1ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር በላይ በየዓመቱ ለወደብ ብቻ በማዋል በድህነት ውስጥ እንድትማቅቅ አድርጓታል:: ኢትዮጵያ ወደብ አልባ በመሆኗ ለኪራይና ለመጓጓዣ ከፍተኛ ዶላር ስለምታፈስ የሸቀጦች ዋጋ እንዲንርና የኑሮ ውድነትም እንዲባባስ ምክንያት ሆኗል::

በዲፕሎማሲ እና በተጽዕኖ ፈጣሪነትም ረገድ የኢትጵያ ሚና አሽቆልቁሏል:: ኢትዮጵያ የምትገኝበት የአፍሪካ ቀንድ በዓለም እጅግ ተፈላጊ ከሆኑትና የሃያላን ሀገራትንም ቀልብ የሚስብ በመሆኑ እድገቷን የማይፈልጉ አካላት በተቀነባበረ ሴራ ከቀይ ባሕር እስኪያርቋት ድረስ ገናና እና በሁሉም ዘንድ ተፈላጊ ሆና ቆይታለች:: ሆኖም ሀገሪቱ ወደብ አልባ ከሆነች ጀምሮ ተፈላጊነቷ አሽቆልቁሏል::

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ወደብ አልባ ከሆኑት16 ሀገራት አንዷ ብትሆንም ወደብ አልባ የሆነችባቸው አመክንዮዎች ግን ታሪካዊም ሆነ ሕጋዊ መሰረት የሌላቸው ናቸው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ 126 ሚሊዮን ደርሷል:: በአጠቃላይም በኢትዮጵያ የሚኖረው ሕዝብ የባህር በር የሌላቸውን ሀገራት ሕዝብ 1/3ኛውን ይሸፍናል::

ይህንን ሕዝብ ቁጥር ያህል ይዞ ደግሞ ባሕር እና ወደብ አልባ የሆነ አንዳችም ሀገር የለም:: ስለዚህም ኢትዮጵያ በባሕር እና ወደብ አልባነት የተጋረጡባትን ችግሮች ለመፍታት ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ በርካታ ጥረቶችን ስታደርግ ቆይታለች:: ይኼው ጥረቷ ፍሬ አፍርቷል:: ታህሳስ 23 ቀን 2016 ዓ.ም ኢትዮጵያና ሶማሊላንድ የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመው ወደተግባር ገብተዋል::

ኢትዮጵያና ሶማሊላንድ ያደረጉት ስምምነት ለኢትዮጵያም ጥቅሙ የጎላ ነው:: ኢትዮጵያ ከ33 ዓመታት በኋላ የባሕር በር የምታገኝበት አማራጭ የሚያሰፋ መግባቢያ ሰነድ (Memorandum of understanding) በኢትዮጵያ እና በሶማሊላንድ መካከል ከተፈረመ በኋላ በኢትዮጵያውያን ዘንድ አዲስ ተስፋ ፈንጥቋል:: ስምምነቱ ለኢትዮጵያም ዘርፈ ብዙ ጥቅም ከማስገኘቱም በሻገር መረጋጋት ለራቀው አፍሪካ ቀንድ አካባቢ በርካታ ትሩፋቶችን ይዞ የሚመጣ ነው ::

ይህ የመግባቢያ ሰነድ ሲተገበር አካባቢያዊ መረጋጋት የሚያመጣና ኢትዮጵያም በቀጣናው ላይ አለኝ የምትለውን የባለቤትነት ጥያቄ መልስ እንዲገኝ በር የሚከፍት ነው:: ቀጠናዊ ሰላምን በማስፈን የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የተረጋጋ እንዲሆን በር ይከፍቷል::

በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ፣ በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ እየተከሠቱ በሚገኙ የጸጥታና የደኅንነት ፈተናዎች የተነሣ የኢትዮጵያ ወጪና ገቢ ንግድ አደጋ እየተጋረጠበት ይገኛል:: በቅርቡ እንኳን የሁቲ አማጺያን በቀይ ባሕርና በኤደን ባሕረሳላጤ አካባቢ በመርከቦች ላይ እየፈጸሙት ባለው ጥቃት ከአካባቢው አልፎ በዓለም የንግድ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን አሉታዊ ተጽዕኖ መገንዘብ ይቻላል::

ስለሆነም ስምምነቱ ኢትዮጵያ ደኅንነቱና አስተማማኝነቱ የተጠበቀ የባሕር በር እንድታገኝና በቀይ ባሕር አካባቢ አጥታው የነበረውን ስፍራ መልሳ እንድታገኝ ከማድረጉም ባሻገር በቀጠናው አስተማማኝ ሰላም እንዲሰፍን ያደርጋል::

በአጠቃላይ ኢትዮጵያና ሶማሊ ላንድ የተፈራረሙት የመግባቢያ ሰነድ ማንንም የሚጎዳ አይደለም:: ይልቁንም አካባቢያዊ መረጋጋት የሚያመጣና ኢትዮጵያም በቀጣናው ላይ አለኝ የምትለውን የባለቤትነት ጥያቄ መልስ እንዲገኝ በር የሚከፍት ነው::

ከሁሉም በላይ ዓለም አቀፍ ሕጉና ተቋማት ጭምር ፍትሃዊ የሆነ የባሕር በር ተደራሽነት እንዲኖር ስለሚፈልጉ በኢትዮጵያና በሶማሊ ላንድ መካከል የተደረሰ የመግባቢያ ስምምነትን የሚደግፉት እና ተቀባይነትም ያለው ነው:: በተለያዩ ጊዜያትም ከሀገራትና ዓለምአቀፍ ተቋማትም የሚወጡት መግለጫዎች ይህንኑ የሚያንጸበርቁ ናቸው::

መንግስት እራሱ ተነሳሽነቱን ወስዶ የኢትዮጵያውያንን የባሕር በር የዘመናት ጥያቄ ለመመለስ በርካታ ጥረቶችን እያደረገ ነው:: ከሶማሊ ላንድ ጋር የተፈረመውም የመግባቢያ ሰነድ የዚሁ ጥረቱ ማሳያ ነው:: ከሶማሊ ላንድ ጋር የተደረሰው ስምምነት የመጀመሪያው እንጂ የመጨረሻው አይደለም:: ሌሎችም የቀጣናው ሀገራት በዚሁ መንገድ ይጓዛሉ ተብሎ ይጠበቃል::

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ለአምራችና ሸማቹ መፍትሔ ይዞ የመጣው ተንቀሳቃሽ የቲማቲም ማቀነባበሪያ

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ የሚያዘጋጃቸው ኤግዚቢሽኖች ዋና የትውውቅና የገበያ ትስስር መፍጠሪያ ስፍራ መሆን እየቻሉ ናቸው። በቅርቡ በሚሊኒየም አዳራሽ በተዘጋጀው የንቅናቄው ኢግዚቢሽን ላይ ከተሳተፉት የጨርቃጨርቅ፣ የቆዳ፣ የግንባታ ግብዓት አምራቾች፤ ማሽነሪ አምራቾች የአውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪዎች፣ የግብርና ምርቶች አቀነባባሪዎች፣ ወዘተ መረዳት እንደተቻለውም መድረኩ የዘርፉን አምራች ኢንዱስትሪዎችና ምርቶቻቸውን ፈላጊዎችን ማስተዋወቅና ማስተሳሰር ችሏል።

ከመድረኩ ጉብኝትና ከተሳታፊዎች መረዳት እንደቻልነውም መድረኩ የትውውቅና የገበያ ትስስር መፍጠሪያ መሆን መቻሉን አረጋግጠናል። ቴክኖሎጂ በማላመድ በኩል እየተከናወኑ ያሉ ተግባሮችንም አመላክቷል። ወደ ኢግዚቢሽኑ አዳራሽ ሳይገባ በስተቀኝ ውጪ ላይ የቀረቡ የሀገር ልጆች አሻራ ያረፈባቸው የማሽንና የአውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪው ምርቶችም ይህንን ያመላከቱ ናቸው።

በዚህ ስፍራም አንድ ግዙፉ ተሳቢ ተሽከርካሪ ላይ የቲማቲም ማቀነባበሪያ የሚል መረጃ በትልቁ ተለጥፎበት ተመለከተን። የተሽከርካሪውን ዙሪያ በሚገባ ከቃኘን በኋላም የተሳቢውን መወጣጫ ተጠቀምን በራፉ ደርሰን፤ ሆድ እቃውንም ቃኘን። የኢትዮ ኢንጂነሪግ ግሩፕ አንዱ አካል በሆነው በቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ የተመረተ የቲማቲም ማቀነባበሪያ ስለመሆኑ የማቀነባበሪያው አስገብኚ ገለጸልን።

ማቀነባበሪያውን እያስጎበኘ ማብራሪያ የሰጠን የቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ ኢንዱስትሪ የጥራት ቁጥጥርና ማረጋገጫ ክፍል ኃላፊ አቶ ግርማዬ ልዑል ሰገድ እንዳብራራው፤ ቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ በርካታ ኢንዱስትሪዎችን በስሩ ያቀፈው የኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ አካል ነው።

ቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ፣ የአዳማ እርሻ መሳሪያዎች ማምረቻ፣፣ ሜክሲኮ ላይ የሚገኘው አዲስ ማሽን ቱልስ፣ ትራንስፎርመር የሚያመርተው ፓወር ኢንጂነሪንግ በዚህ ግሩፕ ስር ከሚገኙት ዘጠኝ ኢንዱስትሪዎች መካከል ይጠቀሳሉ። በደብረ ብርሃንም ማሽነሪዎችን የሚያመርት ድርጅት አለው።

ይህ የቲማቲም ማቀነባበሪያ የተሰራው በቢሾፍቱ አውቶሞቲቭ ነው። በኛ ተቋም ውስጥ ሶስት አይነት ተንቀሳቃሽ የአግሮ ፕሮሰሲንግ ፕላንቶች ሰርተናል የሚለው አቶ ግርማዬ፣ እነዚህም የጥራጥሬና ቅመማ ቅመም፤ የድንች ማቀነባበሪያ እና ይህ የቲማቲም ማቀነባበሪያ መሆናቸውን ይገልጻል።

ለኢትዮ ኢንጂነሪግን ግሩፕ ከመንግስት ከተሰጡት ዋና ዋና ተልእኮዎች መካከል አንደኛው ቴክኖሎጂን በሀገር ውስጥ ማልመድ /አዳብት ማድረግ /ነው። ሁለተኛው ደግሞ ገበያን ማረጋጋት ነው ሲል ጠቅሶ፣ የቲማቲም ማቀነባበሪያው ከዚህ አኳያ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው አስታውቋል።

አቶ ግርማይ እንዳብራራው፤ የቲማቲም አግሮ ፕሮሰሲንግ ፕላንቱ ዋና ዓላማ ገበሬው ያለበት ቦታ ድረስ ተንቀሳቅሶ የቲማቲም ሳልሳና ሌሎች የቲማቲም ውጤቶችን ማቀነባበር ነው። አሁን ባለው ሁኔታ አርሶ አደሩ አካባቢ ያለው የቲማቲም ዋጋ ዝቅተኛ መሆኑን ጠቅሶ፣ ምርት በዝቶ የሚያነሳው አጥቶ የሚጣልበት ሁኔታ እንደነበረም ይጠቅሳል። በዚህ ማሽን የቲማቲሙን የቆይታ ጊዜ /ላይፍ ታይም/ በመጨመር የአርሶ አደሩንም የሸማቹንም ተጠቃሚነት ማሳደግ ይቻላል።

በዚህ ማሽን አራት አካላት ይጠቀማሉ ተብሎ ታስቧል። አንደኛ አርሶ አደሩ፣ ሁለተኛው ሸማቹ፣ ሶስተኛው መንግስት ሲሆኑ፣ አራተኛው ደግሞ በአነስተኛ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝነት ተደራጅተው ከልማት ባንክ ፋይናንስ አግኝተው የሚሰሩ አካላት ናቸው።

ይህን ማሽን ገዝቶ መስራት የሚፈልግ ባለሀብት ካለም ባለሀብቱ ተጠቃሚ ይሆናል ሲል ጠቅሶ፣ ይህን ሲያደርግ እሱ ብቻ አይደለም ተጠቃሚው፣ የሚቀጥራቸው ሰራተኞችም ይጠቀማሉ ብሏል።




**ማቀነባበሪያው በሰዓት 500 ኪሎ ግራም ቲማቲም መፍጨት ይችሳል**

ይህንንም ሲያብራራ እንዳለው፤ አርሶ አደሩ ምርቱ ሲባዛና ተቀባይ ሲያጣ ሲደርስበት ከኖረው ችግር ይታደገዋል። የአርሶ አደሩ ምርት ገበያ ያገኛል። እንደሚታወቀው

ማኅበረሰቡ ቲማቲም ሲረክስ በዝቅተኛ ዋጋ እየገዛ ቢጠቀምም፣ ሲወደድ ደግሞ 120፣ 100 ብር የሚገዛበት ሁኔታ ታይቷል።

የቲማቲሙን የቆይታ ጊዜ /ላይፍ ታይም/ በማራዘም ሸማቹ በተመሳሳይ ዋጋ ሁሌም ቲማቱሙን የሚያገኝበትን ሁኔታ እንፈጥራለን ማለት ነው ይላል። ዋጋው ዝቅ ባለ ጊዜ ትኩሱን፣ ዋጋው ወደድ ሲል ደግሞ የተቀነባበረውን በ20ና 25 ብር እየገዛ እንዲጠቀም ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል ነው ያለው።

ስለ ማቀነባበሪያው የማምረት አቅም ተጠይቆ ሲያብራራም፣ ማቀነባበሪያውን /ፕላንቱን/ ወደ መስራት ሲገባ የተያዘው እቅድ በሰዓት 250 ኪሎ ግራም ቲማቲም እንዲፈጭ አርገን ነው ይላል። የቦይለሮቹንና ሌሎች የማሽኑን ክፍሎች አቅም ጨምረን በሰዓት 500 ኪሎ ግራም ቲማቲም እንዲፈጭ አርገን ሰርተነዋልም ነው ያለው።

ማቀነባበሪያው በተለያዩ የኃይል አማራጮች እንዲሰራ ተደርጎ ስለተሰራ ከኃይል አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሊገጥመው የሚችል ችግር አይኖርበትም። በገጠር አካባቢ መቶ በመቶ መብራት የለም፤ ማቀነባበሪያው የኤሌክትሪክ አገልግሎት ባለበት አካባቢ የሚገባ ከሆነ ከኤሌክትሪክ አገልግሎት ባለሶስት ፌዝ መስመር ጋር ተያይዞ እንዲሰራ ይደረጋል። የኤሌክትሪክ ኃይል ርካሹ ስለሆነ በእዚህ መገልገል ያዋጣል።

ይህ የማይሆን ከሆነ ደግሞ ሌላ የኢነርጂ አማራጭ ተዘጋጅቶለታል። 25 ኪሎ ዋት ጀነሬተር መጠቀም ይችላል። ይህም የኃይል አቅርቦት ሁሉም የማሽኑን ስራዎች እንዲሰሩ ማድረግ ያስችላል። ኢነርጂ ለማምረት የሚያስችል ቦይለርም ተገጥሞለታል። ከ22 እስከ 23 ሊትር ነዳጅ ተጠቅሞ አንድ ሺ ሊትር ውሃ ወደ እንፋሎት /ኢነርጂ መቀየር ይችላል። በእዚህም አንድ ቀን ሙሉ መስራት ይችላል።

የማቀነባበሩ ስራ እንዴት እንደሚፈጸም ሲያብራራም ከሁለት ቦታዎች በስተቀር አጠቃላይ ስራው አውቶሜትድ ነው፤ በቅድሚያ ቲማቲም ወደ ማሽኑ እንዲገባ ከመደረጉ በፊት የተበላሸ ቲማቲም እንዲወገድ ይደረጋል፤ ከፍተኛ ግፊት ያለው ውሃ በመጠቀም ይታጠባል።

ማቀነባበሪያው ፓስቸራይዝ በማድረግ፣ ማሸግ የሚችልም ነው። የመጠቀሚያ ጊዜ ቆይታን ማሳጠርና ማስረዘም በዚህ ማቀነባበሪያ ተጠቀሞ ማምረት የሚፈልገው ድርጅት ውሳኔ ይሆናል። አምራቹ ለአንድ ዓመት የሚቆይ ማድረግ ከፈለገ ለዚህ የሚያስፈልገውን ፓስቸራይዝድ ማድረጊያ ኬሚካል መጠቀም አለበት። ለስድስት ወር ለሶስት ወር ወዘተ ካለም እንዲሁ የኬሚካል መጠኑ ይወስነዋል።

እጅ ከጀርሞች ንክኪ ነጻ አይደለም የሚሉት አቶ ግርማዬ፣ ይህን ለማስወገድ ስራዎች በማሽን ቢሰሩም ለጀርሞች ምንም አይነት እድል ላለመስጠት በሚል ስራው የሚከናወንባቸው የማሽን ክፍሎች ስተራላይዝድ ይደረጋሉ ሲል ያብራራል። አጠቃላይ ስራው አውቶሜትድ ቢሆንም በሰውም ክትትልና ቁጥር ይደረግበታል ነው ያለው።

ማቀነባሪያው የጤና ሚኒስቴር ስታንዳርድ ያሟላ ማሸጊያንም ያካተተ መሆኑን ጠቅሷል። የአንድ ምርት ዋጋ በአብዛኛው ማሸጊያው ላይ ይወሰናል ያለው አቶ ግርማይ፣ ለሌሎች የምንመክረውም ይህን አይነት ማሸጊያ እንዲኖር ነው፤ ከውጪ የሚመጡት የተቀነባበሩ የቲማቲም ውጤቶችም የሚታሸጉት ይህ ማቀነባበሪያ በሚያሽግበት መንገድ መሆኑን ያስገነዝባል።

ሳልሳው የሚታሸግበት ቁስ እንደ አምራቹ ፍላጎት አንደሚወሰንም ተናግሯል። ማቀነባበሪያውን የሚፈልጉ አካላት ማሸግ የምንፈልገው በብርጭቆ ነው፣ በፕላስቲክ ነው፣ በጆሪካን ነው የሚል ከሆነም በጥያቄያቸው መሰረት ማስተናገድ እንደሚቻልም ጠቁሟል። በታሸገው ምርት ማሸጊያ ላይ ምርቱ የተመረተበት ቀንና ዓመተ ምህረት፣ የአገልግሎት ቆይታውን የሚመለከቱ መረጃዎች ይታተማሉ።

አቶ ግርማዬ እንዳብራራው፤ ምግብ መቶ በመቶ ከጀርም ነጻ መሆን አለበት። ,ምክንያቱም 10ሺ አምርተን አንድ ሰው ከታመመ መጀመሪያ ተጠቃሚው አካል ይጎዳል፤ ሁለተኛ አምራቹ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል። ተጠቃሚው የዚህን ኩባንያ ምርት ተጠቅሜ ታምሜያለሁ ካለ መደርደሪያ ላይ ያለው ምርት ብቻ ሳይሆን እየተመረተ ያለው ምርት እንዲሁም አምራች ድርጅቱ ስም ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

ስለዚህ በቲማቲም ማቀነባበሪያው ተመርቶ የታሸገው ምርትም እንዲሁ መቶ በመቶ ስቴራላይዝድ ተደርጎ እንዲወጣ ይደረጋል ሲል ጠቅሶ፣ የታሸገው ምርት በስቲም ስቴራላይዝድ ከተደረገ በኋላ ነው ወደ ፓኪንግ እንዲሄድ የሚደረገው ብሏል።

እኛ መንግስታዊ የልማት ድርጅት ነን፤ ዋናው ተልእኮዋችን ወደ ሀገር ውስጥ ቴክኖሎጂን በማምጣት ማላመድ ነው። በተለይ ደግሞ ባለሀብቱ የማይደፍራቸውን፣ በገባባቸው እከስርባቸዋለሁ የሚላቸውን ቴከኖሎጂዎች በማምጣት የማላመድ ስራ እንሰራለን ያለው አቶ ግርማዬ፣ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ሀገራዊ ፋይዳቸው ከፍተኛ እንደሆነም አስገንዝቧል። መንግስት ያንን ተልእኮ ለኛ ይሰጣል፤ እኛ እንሰራለን፤ እኛ ይህን ስንሰራ የጣልነው ያነሳነው ብዙ ነገር አለ በማለት ማቀነባበሪያውን በማምረት ሂደት ውጣ ውረዶች መታለፋቸውን ጠቅሷል።

አቶ ግርማዬ ‹‹ማቀነባበሪያው የድርጅቱ የመጀመሪያ ምርት/ፕሮቶታይፐ/ ነው። አሁን የማሽን ስራውን ከልማት ባንክ ጋር ለማያያዝ እየተመከረ ነው። ኢንዲስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ጎብኝተውት ከልማት ባንክ ጋር መተሳሰር አለበት ብለዋል፤ ለወጣቶች የስራ እድል ይከፍታል የሚል አቅጣጫም ሰጥተዋል ሲሉም አብራርቷል። የመንግስት ተቋማት ይህን ማመቻቸት ከቻሉ፣ እኛ ሰርተን ብቻ ሳይሆን ሞክረንም፣ ለሀገር ያለውን ፋይዳ ማሳየት ችለናል ብሏል።

ስራው የቅብብሎሽ እንደሆነም ጠቅሶ፣ ከዚያ በኋላም ስራው ውስብስብ መሆኑን ጠቅሶ ተቀናጅተን ሌሎች የመንግስትና የግል ተቋማት እጃቸውን አስገብተው በግል የሚወስዱም ሆኑ የተደራጁ አካላት ሊወስዱት እንደሚችሉ ጠቁሟል።

እሱ እንዳለው፤ የድርጅቱ ዓላማ የቲማቲም ማቀነባበሪያ ማሽን መስራት ብቻ አይደለም፤ ይህን ማሽን እኔም መስራት እፈልጋለሁ የሚል አካል ካለ/ የግልም ሆነ የመንግስት/ ለማቀነባበሪያው /ለፕላንቱ/ ያወጣውን ወጪ ሸፍኖ እንዲወሰድ ተደርጎ ድርጅቱ ሌላ ለሀገር የሚያስፈልግ ፕላንት ወደ መስራት ይገባል።

እነሱ የሰሩትን ማሽን የሚፈልጉ አካላት እየተበራከቱ መምጣቸውንም ጠቅሷል። ‹‹ ይህ ማሽን ጎብኝቶ ያልተደነቀ የለም። ከመቶ በላይ የቢዝነስ ካርዶችን ይዘን መጥተን ነበር፤ ሁሉም በጎብኚዎች ተወስደዋል፤ ሌሎች እጅ ላይ የነበሩ ቢዝነስ ካርዶችን ጭምር ተቀብለን ሰጥተናል። ተቋማችን ድረስ ለመምጣት በመፈለግ ስልክ ቁጥር የወሰዱም አሉ። የመንግሰትም ጽኑ ፍላጎት እንዳለ አስተውለናል ሲል ለማሽኑ በጎብኚዎችና መንግስት ዘንድ ያለው ፍላጎት ከፍተኛ ስለመሆኑ አመልክቷል።

እነ አቶ ግርማዬ አሁን ከገኙት ግብረ መልስ በመነሳሳት ማቀነባበሪያውን ማስፋፋት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ለመስራት ማሰብ ጀምረዋል። ሌሎች ማሽኖችን እንዲሰሩም መነሳሳት ፈጥሮባቸዋል። ከዚህ ባለነሰ እቃና የማምረት ፍጥነትን ከፍ በሚያደርግ መልኩ አንዴት መስራት ይኖርብናል ብለን እንድናስብ አርጎናል ሲል አቶ ግርማዬ ተናግሯል።

ይህ እንዲሆን ግን ለማሽኑ የሚያስፈልጉ ከውጪ የሚመጡ እቃዎች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ያስፈልጋል። ማንኛውም ሀገር በቀል ድርጅት እነዚህን አካላት ማምረት እችላለሁ ካለ ማምረት ይችላል፤ ለእዚህ ግን የምግብና የመድህኒት ማምረቻና መጠቀሚያ እቃዎችን ማምረት ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም ፈቃድ መውሰድ ይኖርበታል።

በመጀመሪያ የሚፈለገው ራስን መቻል ነው፤ እንዱ የውጪ ድርጅት ጥቅሜ ተነካብኝ ባለ ቁጥር ከሚጥለው ማእቅብ ለማውጣት የሀገር ውስጥ የማምረት አቅምን ማሳደግ ያስፈልጋል ሲል አቶ ግርማዬ አስገንዝቧል።

የማቀነባበሪያውን ዋጋ አስመልክቶ ሲያብራራም ሁሌም የመጀመሪያ ምርት ውድ መሆኑን ጠቅሶ፣ ቴክኖሎጂ እየተስፋፈ ሲመጣ የማምረቻ ጊዜና ወጪ እየቀነሰ ስለሚመጣ ዋጋው እየቀነሰ ይመጣል ብሏል።

ብዙ ማሽኖችን ብትታዘዙ ማምረት ትችላላችሁ ወይ የሚል ጥያቄ ያቀረብንለት አቶ ግርማዬ፣ መጀመሪያው የኢንጂነሪግ ስራውን ልታፈርስ ትችላለህ፤ ትገነባለህ፤ ብዙ ጊዜ ሊወሰድ ይችላል፤ ፕሮቶ ታይፑን ለማዘጋጀት አንድ ዓመት አካባቢ ሊወስድም ይችላል ሲል ጠቅሶ፣ ብዙ ማምረት /ማስ ፕሮዳክሽን/ ውስጥ ለመግባት ለኛ ብዙ ችግር የለብንም ሲል አስታውቋል።

ኢትዮ ኢንጂነሪግ ሚሊኔየም ፓርክን የሚያካክሉ ትላልቅ ወደ አምስት የሚደርሱ ፋብሪካዎች እንዳሉት ገልጾ፣ ብዙ ማምረት /ማስ ፕሮዳክሽን/ መቶም አንድም ብንታዘዝ አንድ አይነት ነው ብሏል፤ አንድ ታዞ የሚወጣው አንድ ወር የሚወስድ ከሆነ ለኛ መቶ ብንታዘዝም ያው ነው የሚሆነው›› ሲል አብራርቷል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

## የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ባህሉ ያደረገ ማኅበረሰብን የመፍጠር ጥረት

ምሕረት ሞገስ

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በዋናነት ሰው ወዶ እና ፈቅዶ የራሱን ገንዘብ፣ ጊዜ እና ጉልበት ለሌላ ሕይወት ላለው አካል መስጠት ማለት መሆኑን የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሶሾሎጂ መምህር ዶክተር ታዬ ንጉሴ በበኩላቸው፤ አንድ ሰው ያለውን ዕውቀት፣ ክህሎት እና ማንኛውም ሃብት ለሌሎች ማለትም ለሰው ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ሕይወት ላላቸው እንስሳትም ሆነ ዕፅዋት ደህንነት እንዲጠበቅ የራሱን ድርሻ መወጣት መቻል ማለት ነው ሲሉ ያብራራሉ::

በጎ ፈቃደኝነት አንፃራዊ ቃል ነው:: ለቤተሰብ የሚሰጥ አገልግሎት ጥሩ ቢሆንም፤ እውነተኛ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ከአንድ ሰው ጠባብ ክበብ ውጪ ማገልገልን የያዘ ነው:: ከራሳቸው ከባቢ ወጥተው የሚያገለግሉ ሰዎች አስተሳሰባቸው አድጓል ማለት ይቻላል:: የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ከራስ ጋር በዘር፣ በዝምድና ወይም በሃይማኖት የሚገናኙትን ለይቶ ማገዝ ሳይሆን፤ ማንኛውንም ሕይወት ያለውን ሰው ማገልገል በጎ ፈቃደኝነት ነው::

እንደ ዶ/ር ታዬ ገለፃ፤ በጎ ፈቃደኝነት ከላይ ወደ ታች እና ከታች ወደ ላይ የሚባል አካሔድ አለው:: ከታች ወደ ላይ ቢመጣ መልካም ነው:: ሕዝቡ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ባህል ኖሮት መንግስት ያንን ቢያበረታታ እና ቢያጠናክር ምርጥ ነው:: ሕዝቡ የራሱ ባሕል ካለው ከመንግስት ጫና እና ግፊት ሳይኖር በራሱ ወስዶት የሚሔድበት ሁኔታ ይኖራል:: እነኚህ ዓይነት ነገሮች ከላይ የሚጫኑ ሳይሆኑ ከኅብረተሰቡ ባሕል የሚመነጩ ናቸው:: ሁሉም ሰው በጎ ፈቃደኛ ነው ማለት አይቻልም:: የበጎ ፈቃደኝነት ዝንባሌ ያላቸው ሰዎች አሉ:: ይህንን ዝንባሌ የሚወስነው የስብዕናቸው ከፍታ ነው:: ስብዕና ማለት ደግሞ የሰውየው የስነልቦና አመለካከት ለበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ዝንባሌ አለው ወይስ የለውም የሚለውን ይወስናል:: በሌላ በኩል ከባቢያዊ ሁኔታዎች አሉ:: አንዳንድ ባሕሎች ለበጎ ፍቃደኝነት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ ናቸው ይላሉ::

እንደ ዶ/ር ታዬ ገለፃ፤ ባሕሎች መንፈሳዊ፣ ሃይማኖታዊ እየተባሉ የሚከፋፈሉ ናቸው:: ከባሕል በተጨማሪ እውነተኛ ትምህርትም ሰውን በሳል እና ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት ዝንባሌ እንዲኖረው ያደርጋል:: ስለዚህ የበጎ ፈቃደኝነት ዋናው መሠረት ሰዎች ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች ማሰብ መቻላቸው ነው:: ማለትም ግለኝነት ወይም ስለራስ ከማሰብ እና ከማውጠንጠን በላይ ለሌሎች መጨነቅ ነው:: ይህ ወደ ፍልስፍና ይወስዳል:: እነ ሶቅራጥስ፣ ታላላቅ የሃይማኖት አባቶች እና ቅዱሳን ስለሰው ማንነት የሚገልጹት ነገር አለ:: ራስህን እወቅ ይላሉ:: ሰው የስጋ እና የአጥንት ክምችት የሆነ ስግብግብ ፍጡር መሆኑን ይገልፃሉ:: ነገር ግን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሲታሰብ ሰው የስጋ እና የአጥንት ክምችት የሆነ ስግብግብ ፍጡር ከመሆን በላይ መሆኑ ሲታሰብ፤ ግለኝነትን እየተቀረፈ ይሄዳል::

ነገር ግን ትምህርት ሁሉ ይህን ያደርጋል ማለት አይደለም:: አንዳንድ ትምህርቶች እንዲያውም ራስ ወዳድ ያደርጋሉ:: ነገር ግን ትምህርት ካሪኩለም ውስጥ ሰዎች ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች እንዲያስቡ የሚያደርጉ ጉዳዮች መካተት አለባቸው:: እውነተኛው የምንመኘው ትምህርት ሰዎች ከራሳቸው በላይ ለሌሎች እንዲያስቡ ተደርጎ የተቀረፀ ከሆነ ነው:: ለምሳሌ ሲቪክ ሰዎች ከራሳቸው አልፈው ለሌላው እንዲተርፉ የሚገፋፋ ነው::

እንደ ዶ/ር ታዬ ገለፃ፤ ነገር ግን ከትምህርት ባሻገር ዋናው ሰዎች በግላቸው ራሳቸውን ሲያሳድጉ እና ሲያበለፅጉ እንዲሁም ዓዕምሯቸውን ሲያሰፉ በተጨማሪ ከፍ ወዳለ አመለካከት ሲያድጉ ከጥቃቅን ነገሮች ይልቅ ትልልቅ ነገሮችን ማሰብ ይጀምራሉ፤ ወደ በጎ ፍቃደኝነት ሊያዘነብሉ ይችላሉ:: ስለዚህ እነኚህ ነገሮች በጎ ፈቃደኞችን ይፈጥራሉ የሚል እሳቤ አለ::

ዶ/ር ታዬ ከባህል አንፃር ሲያስረዱ፤ ባሕል የአንዱ አገር ከሌላው አገር፣ የአንዱ ማኅበረሰብ ከሌላው ማኅበረሰብ ይለያል:: ባሕሎች ደግሞ በሁለት ይከፈላሉ:: ቡድናዊ እና ማኅበረሰባዊ የሚባሉ አሉ:: ቡድናዊ በተለይ የማኅበረሰብ ትሥሥር ላይ ትኩረት የሚሰጡ ባሕሎች ለበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ግንዛቤ ያላቸውን ሰዎች ይፈጥራሉ:: ሶሻል ካፒታል የተባለ ፅንሰ ሃሳብ አለ:: ቀመር (ፎርሙላ) አለው:: በእዚህ ቀመር በእዛ ማኅበረሰብ ውስጥ ያለው የስልጣኔ ባሕል (የሲቪክ ካልቸር) የበጎ ፈቃድ ዝንባሌ ጎልቶ እንደሚወጣ ያሳያል:: ይሔ ደግሞ ከመንግስት ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ጋር ሲደጋገፍ የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይቻላል:: በማለት የራሳቸውን ተሞክሮ በምሳሌነት ይጠቅሳሉ::

**መንግስትም በጎ ፈቃደኝነት እንዲሰፋ፤ ከፍተኛውን ሚና መጫወት አለበት:: ካሪኩለምን ከማስተካከል ጀምሮ ሰዎች እንዲነሳሱ እና የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንዲሰጡ ሁኔታዎች ማመቻቸት አለባቸው**

ለትምህርት በሄዱባት ጃፓን እንደተመለከቱት በዩኒቨርሲቲው በመቶ የሚቆጠሩ ክለቦች አሉ:: በትምህርት መጀመሪያ ቀን ተማሪዎች በሌሎች ተማሪዎች ማደሪያቸው ድረስ በመሄድ ለሊቱን ሙሉ እያንኳኩ ተማሪዎችን ይመለምላሉ:: ዩኒቨርሲቲው ውስጥ በእረፍት ሰዓት ጊቢው በጣም ደስ ይላል:: ምክንያቱም ክለቦች ትርዒት ያሳያሉ:: የአካባቢ ጥበቃው የአካባቢ ጥበቃ ሥራ ላይ እየሠሩ ያሉትን ያሳያሉ:: ሰዓሊዎች ስዕላቸውን ያስጎበኛሉ:: እንዲህ ያለ ነገር ሕይወትን ሙሉ እንደሚደርግ ያስረዳሉ::

በተቃራኒው በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ሲያብራሩ፤ አገር ውስጥ ባሉ ዩኒቨርሲቲዎች ረፍት ሲኖር፤ ሰው የሆነ ቦታ ቁጭ ብሎ ከመቆዘም ውጪ ምንም ሲያደርግ አይታይም:: የአካዳሚክ ተቋማቱም በሌላው ዓለም እንደተለመደው የአገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎች ይህንን አያበረታቱም:: እንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ለበጎ ፈቃደኝነት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራሉ::

በተጨማሪ ዶ/ር ታዬ እንደሚያስረዱት፤ ባሕል ብቻ ሳይሆን የመንግስት ፖሊሲ እና ስትራቴጂዎችም ለእዚህ አገልግሎት ምቹ ሁኔታን መፍጠር አለባቸው:: የሲቪክ ባሕል ማለት የሰለጠነ ባህል ማለት ነው:: ይህ ትርጉሙ ለሌሎች መቆርቆር እና ለሌሎች ማሰብ ሌሎችን መርዳት ማለት ነው:: ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ በዘመኒቷ ኢትዮጵያ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ጅማሬዎች አሉ:: ብዙም በጥናት የዳበረ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ባይሆንም ለምሳሌ በቀዳማይ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት በጣም በተደራጀ መልኩም ባይሆን የማኅበረሰብ አገልግሎት በሚል፤ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ያሉ ሰዎችን ፊደል የማስቆጠር ሥራ ይሠሩ ነበር:: እንዲሁም የስካውት ቡድን ነበር::

ለስካውት ቡድን አባላት የዓዕምሮ የአካል እና የሥነልቦና ሥልጠና ይሰጣቸዋል:: እንደ ወታደር ጫካ ገብተው ይሰለጥናሉ:: ወደ ሌሎች አካባቢዎች እየሔዱ ለገበሬው አረም በማረም፣ አነስተኛ የመንገድ ሥራ ይሠራ ነበር:: እዛ ውስጥ የነበሩት በትምህርት የላቁ እና አስተሳሰባቸውም ከፍ ያሉ ነበር:: በኋላም ወደ ፖለቲካው ዓለም የመጡት ብዙዎቹ እነርሱ ናቸው:: ኢህአፓም ሆነ ሌላ ወደ ፖለቲካው የተጠጉ ልጆች መነሻቸው በንጉስ ቀዳማይ ኃይለስላሴ ዘመን የስካውት አባል ነበሩ:: እነዚያ ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች ለመሆን ራሳቸውን ያዘጋጁ ነበሩ:: ነገር ግን ተጠናክረው አልቀጠሉም:: ደርግ አቋረጣቸው::

በሌላ በኩል የበጎ ፈቃደኝነት ሥራ በተጠናከረ መልኩ በደርግ ዘመን በአዋጅ መልክ የዕድገት በሕብረት ዘመቻ እና መሠረተ ትምህርት ተካሂዷል:: ተማሪዎች ከ10ኛ ክፍል ጀምሮ ትምህርት ቤት ተዘግቶ ወደ ገጠሪቷ ኢትዮጵያ በማምራት ሕብረተሰቡን የማደራጀት እና የማሥተማር ሥራ ይሠራ ነበር:: እነኚህ ተማሪዎች ደግሞ ከአካባቢያቸው ወጥተው ይዘምቱ ነበር:: የአዲስ አበባው ሐረር፣ የትግራዩ ሸዋ እየተባለ በጣም የተራራቀ ቦታ ይዘምቱ ነበር:: ያ ዘመቻ የራሱን በጎ አሻራ ጥሎ አልፏል በማለት ካስገኘው ጥቅም መካከል ለምሳሌ ሰዎች ከአካባቢያቸው ወጥተው የሌሎችን ክልሎች እንዲያውቁ ማድረግ ተጠቃሽ ነው ይላሉ:: በሌላ በኩል አሁንም ያሉት ገበሬ ማኅበራት እና ቀበሌዎች የመስተዳድር መዋቅሮች የተመሠረቱት ዕድገት በሕብረት በተማሩ ሰዎች መሆኑን ያስረዳሉ::

በደርግ ጊዜ የነበረው የብሔራዊ ዘመቻም በኋላ በግዳጅ ተጫነ እንጂ በውትድርና ሰዎች በአካል ብቻ ሳይሆን በዓዕምሮም እንዲሰለጥኑ የሚያደርግ ነው:: በኋላ ጦርነት ሆኖ በግዳጅ ተጫነ እንጂ በፈቃድ ሲሆን፤ ውትድርናም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ነው:: በእስራዔል እና በአሜሪካ ሀገራዊ የውትድርና ሥልጠና ማንነትን፣ ዘመናዊ አስተሳሰብን ከራስ በላይ ለሌሎች መሆንን የሚያሳድጉበት መሆኑን ያስረዳሉ:: ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲ ከመግባታቸው በፊት ይሠለጥናሉ፤ በተጨማሪ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ይሰጣሉ:: ይህ ኤርትራም አለ:: ሰዎች ከራሳቸው እና ከቅርብ አካባቢያቸው በላይ ለአገራቸው እንዲያስቡ የሚያደርግ መሆኑን ዶ/ር ታዬ ያብራራሉ::

አሁን ከበጎ ፍቃድ አገልግሎት ጋር ተያይዞ በመንግስት በኩል እየተሠሩ ያሉ ጥሩ ጅምሮች አሉ:: ነገር ግን የተቀናጀ ወጥነት እና ቀጣይነት ያለው ስለመሆኑ እንደሚጠራጠሩ ይናገራሉ:: በበጎ ፈቃደኝነት የተወሰኑ ቤቶችን መገንባት ብቻ ሳይሆን ሕዝቡን ያነቃነቀ ከታች ወደ ላይ የሚሔድ ሥራ መሠራት እንዳለበት ይጠቁማሉ:: ያንንም ቢሆን በትምህርት ቤት በማስተማር እና በመማር ብቻ ሳይሆን በማንበብ በቤተሰብ ደረጃ ጀምሮ የበጎ ፈቃደኝነት ባሕል እንዲዳብር ማድረጉ ጥሩ ነው ይላሉ::

የቤት ግንባታ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ከበጎ ፈቃድ ጋር የተያያዙ ሥራዎች አረንጓዴ ልማትን ጨምሮ መንግስት በተቀናጀ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ቢሄድበት ጥሩ መሆኑን በማስታወስ፤ የአንድ ሰሞን ወይም የተወሰኑ ሰዎች ጉዳይ ብቻ ሊሆን አይገባም የሚል ፅኑ እምነት እንዳላቸው ይጠቁማሉ::

የበጎ ፈቃድ ባሕልን ለማስፋት ዶ/ር ታዬ እንደገለፁት፤ የግለሰቦች የዓዕምሮ ብልፅግና ወሳኝ ነው:: ሰዎች በዕለት ተዕለት በተራ ሕይወት መርካት የለባቸውም:: ለማደግ እና ሌሎችን ለማገልገል ከተራ ሕይወት ከፍ ማለት አለባቸው:: ራሳቸውን በዓዕምሮ ለማበልፀግ፣ ራሳቸውን ለማሳደግ መቁረጥ እና መወሰን ይኖርባቸዋል:: ፍላጎት መምጣት ያለበት ከውስጥ ነው:: ከውስጥ እንዲመጣ የሚረዱ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: መፅሐፍ ሊያነቃቃ ይችላል:: አሁን ቴክኖሎጂውም ስለሚያግዝ የሚያነቃቁ እና ፍላጎቶችን የሚያመጡ የሚያበለፅጉ ነገሮች ላይ ትኩረት ማድረግ አለባቸው::

መንግስትም በጎ ፈቃደኝነት እንዲሰፋ፤ ከፍተኛውን ሚና መጫወት አለበት:: ካሪኩለምን ከማስተካከል ጀምሮ ሰዎች እንዲነሳሱ እና የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንዲሰጡ ሁኔታዎች ማመቻቸት አለባቸው:: ከላይ ፖሊሲ ማውጣት እና የማይፈፀም ስትራቴጂ መንደፍ ዋጋ የለውም:: ዋናው ጉዳይ ማኅበረሰቡ ላይ መሥራት፤ ዕድሎችን መጠቀም መሆኑን በመጥቀስ፤ መንግስት ፍትሃዊ፣ አቃፊ እና ዲሞክራሲያዊ ከሆነ ሰዎች ወደ አካባቢያቸው አስተዳደር በመሄድ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መስጠታቸው አይቀርም:: ይህ ሲሆን ያሉ ማኅበራዊ እሴቶችን ማለትም ከዕድር ጋር የሚቀራረቡ እቁብ እና ሌሎች ማኅበራትን በመጠቀም የበጎ አገልግሎትን ማስፋት ይገባል ይላሉ::

በሴቶች እና ማኅበራዊ ጉዳይ የወጣቶች ዘርፍ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ዓብይ ሀይለ መለኮት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ጥቅምን አስመልክቶ እንደሚያስረዱት፤ አገልግሎት ተቀባዩ በእርሱ ሆነ በመንግስትም ሊከወን ያልቻለው አስፈላጊ የገንዘብ፣ የባለሞያም ሆነ የጉልበት ጥቅም ያገኛል:: የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪዎች በተለይ ወጣቶች ስብዕናቸውን ይገነባሉ:: ሥራን፣ ታዛዥነትን እና አገልጋይነትን ይለማመዳሉ:: የቡድን ሥራን ይለምዳሉ:: አንዱ ዕውቀት ይዞ ሲመጣ፤ ሌላው ጉልበት አንዱ ገንዘብ ሲያዋጣ እና አንዱ የሌላውን ችግር ሲፈታ የሚገኘው ልምድ ትልቅ ነው:: ከአካባቢያቸው ወጣ ብለው የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሲሰጡ የሌሎችን ባሕል ማወቅን ጨምሮ ብዙ ልምዶችን ያገኛሉ::

አቶ ዓብይ የህክምና ባለሞያዎችን እንደምሳሌ በማንሳት፤ የሕክምና ባለሞያዎች በዘርፉ ላይ በፈቃደኝነት አገልግሎት ሲሰጡ ሰፊ ልምድ እንደሚያገኙ ያስረዳሉ:: ሌሎች ባለሞያዎችም በሞያ ደረጃም የሚገኘው ልምድ ቀላል አለመሆኑን ያመለክታሉ::

የኢትዮጵያ መንግስትም ለበጎ ፈቃድ አገልግሎት ቁርጠኝነት ማሳየቱን ያመለክታሉ:: መንግስት ተቋማዊ እስከሚሆን ከመስራት ጀምሮ ኅብረተሰቡ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ባሕሉ እንዲያደርገው እየጣረ እንደሚገኝ ይጠቁማሉ:: የመንግስት ተነሳሽነት ብቻ ሳይሆን፤ በሒደት ሕብረተሰቡም ሙሉ ለሙሉ ሊቀበለው ይገባል ይላሉ:: የተሰጠውን ወይም የተሠራውን የበጎ አገልግሎት ሥራ መቀበል እና መንከባከብ ከሕብረተሰቡ እንደሚጠበቅ በማስታወስ፤ ሥራው ለአገር ሰላምም ሆነ ለኢኮኖሚ ግንባታም የሚኖረው አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑን ያስረዳሉ:: አሁን የቤት ግንባታን ጨምሮ እየተሠሩ ያሉ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥራዎች በጣም ጥሩ መሆናቸውን በማስታወስ፤ ነገር ግን ከዚህም በላይ ሥርዓት ተበጅቶሎት ሊቀጥል ይገባል የሚል እምነት እንዳላቸው ይናገራሉ::

አቶ ዓብይ እንደ ዶ/ር ታዬ ሁሉ ማኅበረሰቡ የበጎ ፈቃድ አገልግሎትን ባሕሉ ማድረግ አለበት ይላሉ:: በሌሎች አገሮች ከአገር ወደ አገር ሔዶ የሕክምና አገልግሎት መስጠትም ሆነ ሌሎች ሞያዊ አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑን አስታውሰው፤ ይህ በኢትዮጵያም እንዲለመድ የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት አለበት ይላሉ:: ለበጎ ፈቃደኞች ዕውቅና መስጠት እና ለወጣቶችም የሥራ ዕድል በተሻለ መልኩ መስጠት ይገባል ይላሉ::

መንግስት ወርዶ ሕብረተሰቡን ለማሳተፍ ከታች ከወረዳ እስከ ፌዴራል መንግስት ድረስ መዋቅር ተቀርጾ፤ በጀት ተይዞ ሠራተኛ ተቀጥሮ እየተሠራ መሆኑን በማመልከት፤ በተለይ በቢሊየን የሚቆጠር ችግኝ መትከልም ሆነ የቤት ግንባታ እንዲሁም ደም ልገሳ እና የክረምት ማጠናከሪያ ሌሎችም የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች ከመንግስት ብቻ ሳይሆን ከማኅበረሰቡም የሚጠበቅ መሆኑን አመልክተዋል::

ማህበራዊ

# ሴቶች

## በሴት ልጆች ጥቃት ዙሪያ የሚታዩ ፈተናዎች

አስመረት ብስራት

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለያዩ ጊዜያት ሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ይሰማሉ። ይህ ጥቃት መልኩን እየቀያየረ ይሂድ እንጂ፤ ማኅበረሰቡ የችግሩን አሳሳቢነት በመረዳት ሊያስቆመው አልቻለም። ለዛሬ የሴቶች ዓምድ በቅርቡ በማኅበራዊ ሚዲያ የሰማነውን ወጣት ቃልኪዳን ባህሩ ታሪክ ይዘንላችሁ ቀርበናል። ይህች ታዳጊ በርካታ ሴቶች ላይ የሚደርሰው ጥቃት ማሳያ ናት። በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ከታዳጊዋ ጥቃት ባሻገር የሕግ ባለሞያ ሴቶች ማኅበር ከጎኗ መሆኑንና አጋርነቱን ያሳየበትን መግለጫም አካተናል።

ቃልኪዳን የ17 ዓመት ወጣት ናት። ታዳጊዋ ጥቅምት 1 ቀን 2014 ዓ/ም ከቤተሰቦቿ ጋር በምትኖርበት ቤት፣ በድጋሚ ደግሞ በመጋቢት 16 ቀን 2016 ዓ.ም በማታውቃቸው ሰዎች ከምትኖርበት አካባቢ ወዳልታወቀ ቦታ ተወስዳ የአስገድዶ መድፈር ተፈፅሞባታል:: በተጨማሪ በባዕድ ነገር በማደንዘዝ እራሷን እንድትስት በማድረግ ጥቃት እንዳደረሱባትና ጥቃት ካደረሱባት በኋላ፤ እንጦጦ ኪዳነምህረት አካባቢ ከመኪና ውረጂ በማለት ጥለዋት ሄደዋል:: በተጨማሪ ለቤተሰቦቿም ሆነ ለራሷ በተደጋጋሚ ዛቻና ማስፈራሪያ በቴሌግራም ፅሁፍ ስለደረሰባቸው ከፍተኛ ስጋት ውስጥ እንደሆነች በማኅበራዊ ሚዲያዎች ሲሰራጭ ተመልክተናል። ይህች ታዳጊ ከደረሰባት ጉዳት በላይ ዛቻና ማስፈራራያው የስነ ልቦና ጫና እያደረሰባት መሆኑንም ተናግራለች።

ይህን በማኅበራዊ ሚዲያ ሲሰራጭ የነበረን መረጃ ከሕዝቡ እኩል የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር (ኢ.ሕ.ባ.ሴ.ማ) በማኅበራዊ ሚዲያ ሲሠራጭ ለማግኘት ችሏል:: ይህ መረጃ እንደደረሰው ስለጉዳዩ ለማወቅ መንቀሳቀስ እንደ ጀመረ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር ጉዳዩን አስመልክቶ በቅድሚያ መግለጫ የሰጠ ሲሆን፤ በስልክ ቤተሰቦቿን እንዳነጋገረ ገልፀዋል:: በተጨማሪ ማኅበሩ ቃልኪዳንን ከቤተሰቦቿ ማለትም ከእናትና አባቷ ጋር ጠርቶ በሚያዚያ 14 ቀን 2016 ዓ.ም. እና በግንቦት 12 ቀን 2016 ዓ.ም. በቢሯቸው ተገኝተው ከመጀመሪያ ጥቃት ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ ሁለተኛ ጥቃት እስከ ተፈፀመበት ጊዜ ድረስ የነበረውን ሁኔታ አስረድተዋል::

ቤተሰቦቿ ስለጉዳዩ እንደተናገሩት፤ በደምብ በመተንተን ውይይት ከማድረግ ባሻገር፤ በፖሊስ እና በጤና ባለሞያዎችም ምርመራ ተደርጎላታል:: ምርመራውን ተከትሎ ማኅበሩ የሕግ ድጋፍ እንዲያደርግ ቢጠየቅም፤ ማኅበሩ ግን በወቅቱ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል ብሎ ያሰበውንና ጥቃቱ በታናሽ እህቷ ላይም ተከትሎ ሊደርስ እንደሚችል በመስጋት ካሉበት የሽራ ቤት መውጣት እንዲችሉ ለሚኖሩበት አራዳ ክፍለ ከተማ ቤት እንዲሰጣቸው የሚጠይቅ የትብብር ደብዳቤ ፅፎላቸዋል::

በተመሳሳይ ለጊዜው የምታርፍበት ጊዜያዊ መጠለያዎችን የማፈላለግና የማነጋገር እንዲሁም የስነ ልቦና ድጋፍ ማግኘት እንድትችል ማመቻቸት የመሳሰሉ እገዛዎችና ስራዎችን ሲሠሩ መቆየታቸውን አስመልክቶ መግለጫ ሰጥተዋል:: የሕግ ድጋፉን በተመለከተ መግለጫ ሰጪዎቹ ጥቆማው ከደረሰበት ቀን አንስቶ ተጠቂ ሁለቱን ጥቃቶች ባመለከተችበት በአራዳ እና ጉለሌ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ በመመላለስ ጉዳዩን ሲከታተል ቆይቷል::

የአራዳ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያም በጉዳዩ ላይ ስልጣን ስላለው ሁለቱን መዝገቦች አጣምሮ እንደሚከታተልና የደረሰበትንም እንደሚያሳውቀን እንደነገራቸው ገልፀዋል:: በተጨማሪም በወቅቱ የሰጡት ምላሽ የተጠቂ የሕክምና ማስረጃ መደፈሯን የማያሳይና በዚህም መነሻ ማድረግ የሚችሉት ነገር እንደሌለ፣ ሆኖም ግን ተጨማሪ ጥቆማዎች ካሉ ተከታትለው ጉዳዩን እንደሚመረምሩ አሳውቀው በነበረበት ሁኔታ የጉለሌ ክ/ከተማ ፖሊስ መምሪያ መዝገቡን ለአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን እንዳስተላለፈና ኮሚሽኑ እየመረመረ እንደሆነ የበለጠ መረጃ ከኮሚሽኑ ማግኘት እንደሚችሉ ተነግሯቸዋል::



በዚህም መነሻ ከኮሚሽን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ለመነጋገር ያደረጉት ጥረት በስብሰባ ምክንያት ሊሳካ አልቻለም ሲሉ በመግለጫው ተናግረዋል::

ግንቦት 21 ቀን 2016 ዓ/ም፤ በወጣት ቃልኪዳን ባሕሩ ላይ በተፈጸመው አስገድዶ መድፈር፣ ዕገታና ፆታዊ ጥቃት ዙሪያ የወጡ የፖሊስ፣ የሕክምና እና የማኅበራዊ ሚዲያ መረጃዎች እንደገና እንዲጣሩና ትክክለኛው መረጃ ለሕዝብ እንዲደርስ፤ ተጠቂዋም ትክክለኛ ፍትህ እንድታገኝ በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበርና አጋር ድርጅቶች የተሰጠ የጋራ መግለጫ የተለያዩ ማሳሰቢያዎች እነ ጥሪዎችን አካቶ ቀርቧል::

ማኅበራዊ ሚዲያዎች የተበደለን ሰው በደል ከማውጣት እና አስፈላጊውን ምላሽ እንዲያገኝ ከማድረግ አኳያና ድምፁ ያልተሰማ ሰው አገልግሎት ለማግኘት ፈልጎ መረጃው ከሌለው አስፈላጊውን ድጋፍ የሚያገኝበትን የጥቆማ አገልግሎት የመስጠት ሚና መጫወቱ እንዳለ ሆኖ፤ ባልተጨበጠ መረጃ ላይ በመመስረትና ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ሲባል የሚናፈሱ አሉባልታዎችን በመፍጠርና ተጠቂ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ሳያገናዝቡ የተዛቡ መረጃዎችን ማስተላለፍ አንዲት ጥቃት የደረሰባት ሴት መፍትሄ ወይም ፍትህ እንዳታገኝ እንቅፋት ከመሆኑም በላይ በተጠቂ የወደፊት ሕይወት ላይም ከፍተኛ ስነልቦናዊ ጉዳት የሚያስከትል ችግር ሊፈጥሩ ስለሚችል በሕግ ተጠያቂ እንዲሆኑ መደረግ ይኖርባቸዋል ብለዋል::

ፖሊስ በመጀመሪያ ተማሪ ቃልኪዳን ጥቃት ደረሰብኝ ብላ ባመለከተችበት ወቅት በቀጥታ ወደ ሆስፒታል ወስዶ እርዳታ እንድታገኝ ማድረጉ መልካም ሆኖ ሳለ፤ የሕክምናው ሂደት ትክክል መሆኑን ማጣራት፤ ማረጋገጥና ተከታታይ የጤና ክትትል እንድታደርግና የተገኘውን ውጤት ከቤተሰብና ከተጠቂዋ ጋር በግልጽ ከመነጋገር ይልቅ በደፈናው ክትትል እየተደረገበት እንደሆነ ነግሮ የፖሊስ ምርመራው የደረሰበትን ደረጃ በግልፅ ለተጠቂ ማሳወቅና የፖሊስ ምርመራ መዝገቡ የተዘጋም ከሆነ ፋይሉ የተዘጋበትን ምክንያት፣ መዝገቡ የተዘጋው ለጊዜው ቢሆን እንኳን በቂ ማስረጃ ከተገኘ ሊከፈትና ምርመራው ሊካሄድ እንደሚችል ማስረዳት ሲገባ ይህንን ሳያደርግ በመቅረቱ በተጠቂዋ ላይ ተጨማሪ ጥቃት ሊፈጸም ችሏል ብሏል::

ሁለተኛው ጥቃት ሲፈፀም ለሕክምና ጴጥሮስ ሆስፒታል ሄዳ የተደረገላት ሕክምና እና የተመረዘችበትን ሁኔታ ካለ ሳይረጋገጥ፤ መደፈሯንና አለመደፈሯን ብቻ ቅድመ ሁኔታ በማድረግ አስፈላጊው ምርመራ እና ክትትል ሳይደረግ፤ እንደ መጀመሪያው ጥቃት ግልጽነት በጎደለው መልኩ ለተጠቂ በቂ መረጃ ሳይሰጣት በድጋሚ ጉዳዩ ተይዞ የነበረው ሚኒሊክ ሆስፒታል ስለሆነ ወደዛ እንድትሄድና ምርመራ እንዲካሄድ መደረጉ፣ ብትሄድም ፋይሉን ከማገናኘት ውጪ ተገቢው የጤና ምርመራ አለመደረጉ ተጠቂዋ ተስፋ እንድትቆርጥ አድርጓታል::

ፖሊስም መነሻውን የሕክምና ሰነድ ብቻ በማድረግ በጉዳዩ ላይ በቂ ማስረጃ የለም ማለቱ፣ አጥቂዎችን ለመያዝ በቂ ክትትል አለማድረጉ፣ በቴሌግራም፣ በስልክ እንዲሁም በፅሁፍ ለተጠቂ እና ለእናቷ በደረሳቸው መልዕክቶችና ዛቻ ዙሪያ ተጠቂን ፅሁፍ እንድትጽፍ በማድረግና ፅሁፉን በማመሳሰል ብቻ በተለየ የፎረንሲክ ምርመራ ሳይደረግ እንደውም ተጠቂን ተጠርጣሪ የማድረግ በሚመስል ሁኔታ ምርመራውን ማካሄዱ፤ ሌሎች ተጨማሪ የፖሊስ ምርመራ ሂደቶች ተደርገው ቢሆን እንኳን ውጤቱን በግልፅ ለተጠቂም ሆነ ለቤተሰቦቿ ሳያሳውቁ፣ ከወንጀሉ ውስብስብነት እና ተጠቂ በባዕድ ነገር ከመመረዟ በመነሳት የተፈጠረውን ሁኔታ ፖሊስ በረቂቅ ምርመራ ሂደት ከመመርመር አኳያና አስፈላጊውን የፎረንሲክ ምርመራና በመረጃና ደህንነት ተቋም በኩል በወጣት ቃልኪዳን ባህሩ ላይ በተፈጸመው አስገድዶ መድፈር፣ ዕገታና ፆታዊ ጥቃት ዙሪያ የወጡ የፖሊስ፣ የሕክምና እና የማኅበራዊ ሚድያ መረጃዎች እንደገና እንዲጣሩና ትክክለኛው መረጃ ለሕዝብ እንዲደርስ፤ ተጠቂዋም ትክክለኛ ፍትህ እንድታገኝ በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበርና አጋር ድርጅቶች የጋራ መግለጫ ሰጥተዋል።

የቴክኖሎጂ ምርመራ ሳያደርግ ተደርጎም ከሆነ በግልፅ ሳያሳውቅ ተጠቂዋን ሀሰተኛ መረጃ አሰራጭታለች ብሎ መወንጀሉ የምርመራ ሂደት ስነስርዓቱን ተዓማኒነት ከማሳጣት እና አንዲት ጥቃት ለደረሰባት ሴት ፍትህ የመጠየቅና የማግኘት መብቷን ከመንፈግ ባሻገር በሚደረገው ምላሽ አሰጣጥ አገልግሎት ላይ ዝቅ ያለ ግምት እንዲኖራትና አጥቂዎችን የበለጠ ረቂቅ የጥቃት መንገድ እንዲጠቀሙ የሚያበረታታ ከመሆኑም በላይ ጥቃት የሚደርስባቸው ሴቶች ሰሚ አካል እንደሌላቸው እንዲያስቡ የሚያደርግ እርምጃ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል ብለዋል::

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር እና ከታች የተዘረዘሩ አጋር ድርጅቶች የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በጉዳዩ ላይ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ጥሪ እንደሚያቀርቡ ተናግረዋል:: ለአዲስ አበባ ፖሊስ፡ በቴሌግራም መልዕክቶችን እንዲሁም ለተጠቂ እናት በስልክ ሲደርሳቸው የነበረው ዛቻና ማስፈራሪያና የመደራደር ሀሳብን አስመልክቶ ፖሊስ በምን መንገድ አስፈላጊውን ምርመራ እንዳደረገ ከምርመራው ያገኘውን ውጤት በግልፅ እንዲያሳውቀን ይህ አይነት የተወሳሰበ ወንጀል በቴክኖሎጂ፣ በፎረንሲክ እንዲሁም በልዩ ልዩ የፕሮፌሽናል ማስረጃ በማረጋገጥ የሚፈታ ወንጀል በመሆኑ የአዲስ አበባ ፖሊስ ይህን አድርጎ ከሆነም ውጤቱን በግልፅ እንዲያሳውቀን ሲሉ ገልፀዋል:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ ከሆነ ሌሎች ሴቶች ልጆች እንዲሁም ሕፃናት ላይ ከፍተኛ የደህንነት ስጋት የሚያደርስ ከመሆኑ አንፃር አሁንም በድጋሚ ጥልቅ ምርመራ እንዲያደርግ፣ የፖሊስ የምርመራ ሂደት መዝገብ ከወንጀሉ ውስብስብነት አኳያ ለተጠቂ የተደረገ ጥንቃቄም ግልፅነትን መሠረት ያደረገ ስራ ተሰርቶ ከሆነ ሂደቱን እንዲያረጋግጥላቸው አሳስበዋል::

ለሚኒሊክና ለጴጥሮስ ሆስፒታሎች፡ የህክምና ማስረጃውን በሚመለከት ተጠቂ የህክምና እገዛ ይደረገልኝ ብላ እንዳመለከተች ምንም አይነት የዘረመል ምርመራ አለመደረጉ እና በወቅቱ በነበረው የህክምና ባለሙያ በአይን ከመመልከት የዘለለ ህክምና እንዳልተደረገ እና ምርመራው ምን ያህል ደረጃውን የጠበቀ እና የተጠቂን የጉዳት መጠን ያማከለ መሆኑን ለተጠቂ እና ለቤተሰቦቿ በግልፅ ማስረዳትና ተከታታይ ህክምና የሚያስፈልጋት ቢሆን እንኳን እርዳታና የተጠቂን ጤና፣ ጥቅምና ሞራል ያላማከለ የህክምና እገዛ ተደርጎላት ሊሆን እንደሚችል ያሳያል ብለዋል::

በመሆኑም በዚህ ረገድ ለፖሊስ ከተሰጠው የህክምና ማስረጃ ሰርተፍኬት በዘለለ የተደረገላት ህክምና እና የምርመራውን ሂደት በግልፅ የሚያሳይ ውጤት እንዲገለፅላቸው፤ የተጠቂዋን ደህንነት እና የደረሰባት ጉዳት ካለም በግልፅ እንዲያሳውቃቸው ጠይቀዋል::

ለማህበራዊ ሚዲያ አንቂዎች፡ በማህበራዊ ሚዲያ በተደጋጋሚ እየተሰራጨ ያለው ሀሰተኛ መረጃ ተጠቂዋን ከደረሰባት ጥቃት በተጨማሪ ፍትህ የማግኘት መብቷን እየነፈጋትና በጤንነቷም ሆነ በስነልቦናዋ ላይ በድጋሚ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚፈጥርባት በመሆኑና ድጋሚ ሌላ ተጨማሪ ጥቃት ከማድረስ የማይተናነስ በመሆኑ በወጣት ቃልኪዳን ባህሩ ላይ በተፈጸመው አስገድዶ መድፈር፣ ዕገታና ፆታዊ ጥቃት ዙሪያ የወጡ የፖሊስ፣ የህክምና እና የማህበራዊ ሚድያ መረጃዎች እንደገና እንዲጣሩና ትክክለኛው መረጃ ለህዝብ እንዲደርስ፤ ተጠቂዋም ትክክለኛ ፍትህ እንድታገኝ በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበርና አጋር ድርጅቶች የሚጠይቁ መሆኑ በመግለጫው ተጠይቋል።

ለሚዲያ አካላት፡ ሚዲያዎች መረጃዎችን ለኅብረተሰቡ በማሰራጨትና ተደራሽ በማድረግ የአንበሳውን ድርሻ ስለሚወጡ ይህ መረጃ ሃሰተኛ ይሁን አይሁን ለማጣራት በሚደረገው ሂደትና ተጠቂዋ ትክክለኛ ፍትህ እንድታገኝ በሚያደርጉት ጥረት ከጎናቸው በመቆም ትክክለኛውን መረጃ ለኅብረተሰቡ እንዲያደርሱ ጥሪያቸውን አቅርበዋል::

በሴቶች መብቶች ዙሪያ ለሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በየጊዜው በሴት እህቶች ላይ የተለያዩ ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች እየደረሱ ይገኛሉ:: በመሆኑም ስለተጠቂ ቃልኪዳን ባህሩ እየተሰራጨ ያለውን መረጃ ትክክለኛነት በማጣራትና በነበሩ ሂደቶች ዙሪያ የተደረገላት የሕክምና ሂደቶች ትክክለኛነት ተጣርቶ ፍትህ እስኪታገኝ ድረስ ከተቋማቸው ጋር ተባብረው እንዲሰሩ ጥሪ አቅርበዋል::

ለመላው የኅብረተሰብ ክፍል፡ የሴትን ልጅ ጥቃት ፍጹም የማይታገስ ህብረተሰብ እንዲፈጠር ለማህበረሰቡ ግንዛቤ በመስጠት በሚያደርጉት ጥረት ከጎናቸው እንዲቆሙና በማህበራዊ ሚዲያም ሆነ በማንኛውም መንገድ የሚሰራጩ መረጃዎችን ትክክለኛነት ሳያረጋግጡ እንዳይወናበዱና በሀሰተኛ መረጃ ላይ ተመርኩዘው ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶች ስም በጥፋት ከመፈረጅ እንዲቆጠቡ አሳስበዋል::

ይህንን መግለጫ ያስተላለፉ ተቋማት ዝርዝር የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶች ማኅበር የኢትዮጵያ ሴቶች መብት ተሟጋች፤ የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት፤ ሴቶች ይችላሉ፤ ሲሃ ኔትወርክ ናቸው።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**እየሩስ ተስፋዬ**

የዘመናትን መልክ ለማሳየት በጽሑፍ ያሉ ሰነዶች ድርሻቸው ከፍተኛ ነው። አዲስ ዘመን ጋዜጣም ባለፉት ሰማንያ ሦስት ዓመታት የየዘመኑን መልኮች ፍንትው አድርጎ ለአዳዲስ ትውልድ በማሳየት ዛሬ ላይ ደርሷል። ቆየት ካሉ ዓመታት የተለያዩ ዜናዎች እስከ አዝናኝ ጉዳዮች በጋዜጣው የተዳሰሱ አንዳንድ ፅሁፎችን ዓመታትን ወደ ኋላ ተመልሰን በጥቂቱ እናስታውስ።

### ክፍያው በዝቷል

ለግሼ ወረዳ የሚሰጠውን ርዳታ የሚያመላልሱት የጭነት መኪኖች በዚያ ጠመዝማዛ መንገድ ከጭነቱ ላይ ሰው ጭነው መሔዳቸው ለእርዳታ እስከሆነ ድረስ ይደገፋል ነገር ግን ለጫኑበት ዋጋ የሚቀበሉት ገንዘብ አለቅጥ የበዛ ነው።

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ ጥር 29/77 ወደ ራቤል በሚጓዝበት ወቅት ሹፌርና ረዳት የተመኑትን ስድስት ብር መክፈል ስላልቻለ መሀል መንገድ ላይ እንዲወርድ ሆነ ለዚያውም አራት ብር ከፍሏል። የወረደበት ቦታ ከተሳፈረበት በግምት 45 ኪሎ ሜትር ሲሆን ከዚያ በኋላ በእግሩ ከሄደ ከአምስት ሰዓት በላይ ይወስድበታል። አንዳንዶቻችን ለመለመን ብንሞክር እኛም እንዳንወርድ አስጠነቀቀን። ምነው ትንሽ ዋጋው አልበዛም ብዬ ረዳቱን ብጠይቀው « ያልፈለገ በእግሩ መሔድ ይችላል።» አለኝ። እስከተቻለ ድረስ ማሳፈሩን ጥሩ ሆኖ ሳለ በመንግሥት ርዳታ መኪና ለተወሰኑ ሰዎች ጥቅም 98 ኪ. ሜትር ስድስት ብር ማስከፈል እጅግ ይቆጠቁጣልና ጉዳዩ የሚመለከተው ክፍል አስቸኳይ መፍትሄ ይፈልግለት።

**- እሸቴ አሰፋ**

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 05 ቀን 1977 ዓ.ም)**

### ደን ጨፍጭፈው ያቃጠሉ ተቀጡ

በኢሊባቦር ክፍለ ሀገር በደዴሳ ወረዳ ውስጥ ደን ጨፍጭፈው በእሳት ባቃጠሉ ሦስት ግለሰቦች ላይ የወረዳው ፍ/ቤት በድምሩ አንድ ሺ ብር እንዲቀጡ በይኖባቸዋል።

ሙሉነህ ለማ፤ አስረስ ለማና ሽምሱ አባ ቡልጎ በተባሉት ግለሰቦች ላይ ቅጣቱ ሊወሰንባቸው የቻለው አንደኛው ከሳሽ የጥንስስ አምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር ሁለተኛውና ሶስተኛው ደግሞ የቀበሌ ገበሬ ማሕበር የቁጥጥርና የኢሠማ ኮሚቴ ሊቃነ መናብርት ሆነው ሳለ መንግሥት ስለደን ያወጣውን ሕግ በመተላለፍ ጭፍጨፋ በማካሄዳቸውና በማቃጠላቸው መሆኑ ታውቋል።

በዚሁ መሠረት ፍርድ ቤቱ የእያንዳንዳቸውን ጥፋት ከመረመረ በኋላ በአንደኛው ተከሳሽ ላይ 500 ብር መቀጫ ወይም ስድስት ወር እስራት በሁለተኛው ተከሳሽ ላይ 300 ብር መቀጫ ወይም አራት ወር እስራት በሶስተኛው ተከሳሽ ላይ ደግሞ 200 ብር መቀጫ ወይም ሶስት ወር እስራት ወስኖባቸዋል።

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 8 ቀን 1977)**

### የቴሌቪዥኖች ጉዳይ ከአዘጋጅዋ ፤

የቴሌቪዥን አገልግሎት በሀገራችን መሰጠት ከጀመረ ከ20 ዓመት በላይ ሆኖታል። ሆኖም እስከ ጥቂት ጊዜ ድረስ የስርጭቱ አገልግሎት በጥቂት ከተሞች ብቻ የተወሰነ ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን በአብዛኛው የሀገሪቱ ከተሞች እየተዳረሰ ነው። ስለዚህም ዛሬ አብዛኛው ሕዝባዊ ድርጅቶች ቴሌቪዥን እየገዙ ሕዝብ ወቅታዊ ነገሮችን እንዲከታተል፤ ትምህርት እንዲያገኝ፤ እንዲሁም እንዲዝናና ለማድረግ በአመቺ ቦታዎች ላይ በማዘጋጀት ግልጋሎት እየሰጡ ናቸው። ለዚህም የሰበታ ከተማ አጠቃላይ ም/ቤት ተግባር እንደምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል።

በአንጻሩ ግን በሕዝብ ገንዘብ ተገዝተው ለሕዝብ አገልግሎት መስጠት ያለባቸው ቴሌቪዥኖች አንድ ሰሞን በወረት እንዳሉ ለሕዝብ በተከታታይ ቀናት ማገልገል ጀምረው አናሳይም እስከማለት የደረሱ መኖራቸውን ከአንዳንድ ጠቋሚዎች ለመረዳት ችለናል።

ምናልባት ሕዝባዊ ድርጅቶች ለቴሌቪዥኖች በጥንቃቄ መያዝ በማሰብ ያደረጉት ከሆነ መልካም ነው። ግን ለቴሌቪዥኑ ደኅንነት አንድ ሰው በሰዓቱ ከፍቶና ዘግቶ ፕሮግራሙን ለሚከታተለው ኗሪ አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ ረገድ መተባበር ይገባቸዋል እንላለን።

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 11 ቀን 19 77 ዓ.ም)**

### የጆሮ ኩክ ምስጢር

ሁላችንም ብንሆን አብዛኞቻችን እንደሰማነው ወይንም ከመጽሐፍ አንብበን እንደተረዳነው ጆሮ ውስጥ የሚገኝ ኩክ ወደ ውስጥ የሚገባ አቧራ ወይንም ሌሎች ባዕድ ነገሮችን እየጠበቀ በማስቀረት ጆሮአችንን ከአደጋ ይከላከላል። ሆኖም ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጆሮ ኩክ ሌላ ምስጢር ይዞ ተገኝቶአል። የሶቪየት ሳይንቲስቶች ባደረጉት ጥናት መሠረት በጆሮ ውስጥ የሚገኘው ኩክ ዓይነት የሰዎች ዘርን አመጣጥ ለማወቅና የዘራቸውንም ዓይነት ከየትኛው እንደሆኑ ለመመደብ እንደሚረዳ ደርሰውበታል።

በሳይንቲስቶቹ ጥናት መሠረት ኩክን ደረቅና እርጥብ በማለት የመደቡት ሲሆን ለምሳሌ የሞንጎሎይድ ዝርያ የሆኑ ሕዝቦች (ጃፓን ኮርያ ቻይና ወ--ዘ-ተ) በጆሮአቸው ውስጥ ያለው የኩክ ዓይነት በአውስትራሊያና በአፍሪካ ሕዝቦች ውስጥ ሊገኝ ችሏል። የዚህም ጥናት ዋና ዓላማ የሰዎችን የተለያዩ በሽታዎችን የመቋቋምና ያለመቋቋም ባህሪ ለማጥናት እንደሆነም ሳይንቲስቶቹ ገልፀዋል።

**-ዳምጠው ዘገርጂ**

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 3 ቀን 1980 ዓ.ም)**

### አወይ ሞኝ መሆን!

ከንጉሤ አክሊሉ (ሎተሪ)

ለሥራ ጉብኝት - ፈረንጅ አገር ሄጄ
ከሱቅ ውስጥ አይቼ - ሙሉ ልብስ ወድጄ
ትንሽ ቀረብ ብዬ - ዋጋውን ባስተውለው
ሰባት ከሃምሳ ነው - እንቅጩን የሚለው
በጉልህ ተጽፎ - ለዓይን የሚነበበው።
በሰባት ከሃምሳ - ሙሉ ልብስ አግኝቼ
አጋጣሚው ገርሞኝ - በጣም ተደስቼ
ገብቼ ለካሁት ከቦታው አንስቼ።
ግና ይህን ስታይ - ፈረንጅቱ ጮኸች
ገጿን ሦስት ጊዜ - ደጋግማ አማተበች።
እኔም በሷ አድራጎት - በጣሙን ደንግጬ
‹‹ጎትስ ሮንግ›› ብዬብል - ዓይኖቼን አፍጥጬ
እንደው ዝም ብትለኝ ፤መላው ቢጠፋብኝ
ምክንያቱን ለማወቅ - ልቤ ገፋፋኝ።
ሌላ አንድ ሰው መጥቶ - ተጠግቶ አወራት
በገዛ ቋንቋዋ - ደጋግሞ አናገራት።
ስለኔም አድራጎት - ለካስ ነግሯት ኖሮ
ገልመጥ አደረገኝ - ግንባሩን ቆጣጥሮ
በእንግሊዝኛ ቋንቋ - ጠየቀኝ በአንክሮ።
የደረሰብኝን በግልጽ - ሳጫውተው
ምክንያቱን እንጃ! - ሳቅ አንከተከተው
ለካስ የገባሁት - ከልብስ ሱቅ ሳይሆን
ላውንደሪ ቤት ነው - አወይ ሞኝ መሆን!

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 4 ቀን 1980 ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ



## ቻይና ዓይነ ስውራንን መንገድ የሚመራ ባለ 6 እግር ሮቦት ሠራች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የቻይናው ሻንጋይ ጂአዎ ቶንግ ዩኒቨርሲቲ ዓይነ ስውራንን መንገድ የሚመራ አዲስ የሮቦት ቴክኖሎጂ አስተዋውቋል።

ባለ 6 እግሩ ሮቦት መንገድ ጠቋሚ ሴንሰር፣ የሌዘር ራዳር ቴክኖሎጂ እና የናቪጌሽን ሲስተም የተገጠመለት ሲሆን ከሰው በሚሰጠው የድምጽ ትዕዛዝ ካሰቡት ቦታ ያለምንም ችግር ማድረስ የሚችል ነው ተብሏል።

ከቴክኖሎጂው ፈጣሪዎች መካከል አንዱ የሆኑት ፕሮፌሰር ጃው ፌንግ ሮቦቱ በተለይ ለጉዞ ዓይንን ተክቶ ማገልገል የሚችል ነው ብለውታል።

የትራፊክ መብራቶችን እና ሌሎች የደህንነት ማስጠንቀቂያዎችን ጠንቅቆ የሚያውቀው ሮቦት በተጨማሪም አስቸጋሪ የመንገድ ላይ ሁኔታዎችን በመለየት ዓይነስውራን በመንገድ ላይ ከሚያጋጥማቸው አደጋ ይከላከላል ተብሎለታል።

ሮቦቱ በሚኖርበት ከተማ ላይ ያሉ ቤተመጽሀፍቶች፣ የመንግሥት ተቋማት፣ ቤተእምነቶችን እና ሌሎችንም በኢንተርኔት አማካኝነት መዝግቦ የሚያስቀምጥ ሲሆን ከሰዎች በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መጓዝ የሚችል ነው።

የቴክኖሎጂው ባለቤቶች ሮቦቱ የተገጠሙለት 6 እግሮች መሰናክሎችን እና የማይመቹ መንገዶችን እና ደረጃዎችን ያለ ችግር እንዲጓዝ የሚያደርጉት ነው።

ከዚህ ባለፈም በተመጠነ የጉዞ ፍጥነት በሰከንድ 3 ሜትሮችን መጓዝ የሚችል ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ባለቤቱ በሚፈልገው የጉዞ መጠን እንዲፈጥን አልያም እንዲዘገይ የሚነገረውን ትዕዛዝ ይቀበላል።

በተጨማሪም ዓይነ ስውራን የጤና ችግር እና ድንገተኛ አደጋ ሲያጋጥማቸው በተገጠመለት አላርም የርዳታ ጥሪን ማድረግ ይችላል።

እንደ ሲጂቲኤን ዘገባ ከሆነ በቻይና 17.31 ሚሊዮን ዓይነ ስውራን የሚገኙ ሲሆን በተለምዶ ዓይነ ስውራን ከሚጠቀሙት መንገድ ጠቋሚ በትር (ኬን) ባለፈ የሠለጠኑ ውሾችን ለመንገድ መሪነት ይጠቀማሉ፡፡ ሆኖም በአሁኑ ወቅት በቻይና የሚገኙት የሠለጠኑ ውሾች ቁጥር 40 ሺ ብቻ ነው።

እነዚህ ውሾች ለሥልጠና እና ተያያዥ ጉዳዮች ከሚጠይቁት ወጭ አንጻር አዲሱ የሮቦት ቴክኖሎጂ ወደ ገበያ ሲገባ ተመራጭ እንደሚሆን ተነግሯል።

ሮቦቱ በአሁኑ ወቅት የመስክ ሙከራ ላይ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ለገበያ ገና ባያቀርበውም 20 ትእዛዞችን መቀበሉን ገልጿል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ 50 ሚሊዮን ዓይነ ስውራን እንዳሉ ይነገራል ከዚህ ውስጥ 85 በመቶዎች ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ የተለያዩ አደጋዎች ያጋጥሟቸዋል።



## በህንድ በከፍተኛ ሙቀት ሳቢያ የ50 ሰዎች ሕይወት አለፈ

በህንድ ባለፉት 4 ቀናት ውስጥ በከፍተኛ ሙቀት ሳቢያ ከ50 በላይ ሰዎች መሞታቸው ተገለጸ።

በሀገሪቱ ያጋጠመውን ከፍተኛ ሙቀት ተከትሎ 33 ገደማ ሰዎች በሰሜናዊዋ ኡታህ ፓርዴሽ ክልል ውስጥ ሕይወታቸው ያለፈ ሲሆን፤ በኦዲሻ ደግሞ 20 ገደማ ሰዎች በሙቀት ሳቢያ ሕይወታቸው አልፏል።

በህንድ በየዓመቱ በከፍተኛ ሙቀተ ከሚጠቁ ሀገራት መካከል ስትሆን፤ የዘንድሮው ግን ከዚህ ቀደም ከነበሩት ክብረወሰን የሰበረ ነው ተብሏል።

የህንድ ጤና ሚኒስቴር ባወጣው መግለጫ፤ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ባጋጠመው ከፍተኛ ሙቀት ሳቢያ ከ56 በላይ ሰዎች በስትሮክ ተጠቅተው ሕይወታቸው አልፏል።

ባለፉት ሶስት ወራ ማለትም ከመጋቢት እስከ ግንቦት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ 24 ሺህ 849 በላይ ህንዳውያን በስትሮክ ህመም መጠቃታቸውን ነው የጤና ሚኒስቴሩ ያስታወቀው።

የህንድ ጤና ሚኒስቴር ይህንን ቢልም በሙቀት ሳቢያ በስትሮክ የተጠቁ እና ሕይወታቸው ያለፈ ሰዎች ቁጥር ከዚህም ሊልቅ እንደሚችል ተነግሯል።

በሙቀቱ ሳቢያ በርካታ የምርጫ አስፈጻሚዎችም ሕይወት አልፏል የተባለ ሲሆን፤ በተለይም በኡታህ ፓርዴሽ ፖሊስ፣ የምርጫ ጣቢያ ኃላፊ እና የምርጫ ጣቢያ ሠራተኞች በሥራ ላይ እያሉ ከሞቱት መካከል ናቸው።

በከባድ ሙቀት ምክንያት ሕይወታቸውን የሚያጡ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ የመጣ ሲሆን፤ በአሜሪካ እና ህንድ ከባድ ሙቀት ከሚጠቁ ሀገራት መካከል ቀዳሚዎቹ ናቸው።

ባለፈው ዓመት ከ62 ሺህ በላይ ሰዎችን ሕይወት የቀጠፈው ከባድ ሙቀትና ወበቅ በዚህ ዓመትም ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ ነው ተብሏል።

# ስፖርት





## ሚዲያው የስፖርት ተቋማት አሰራርን ሊፈትሽ ይገባል

ዓለማየሁ ግዛው

ስፖርት አሁን ከደረሰበት የእድገትና ዘመናዊነት ደረጃ ላይ እንዲገኝ መሰረታዊ ለውጥ ካመጡ ጉዳዮች መካከል የመገናኛ ብዙኃን ሚና ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል:: እአአ 1990ዎቹ አጋማሽ አንስቶ የመገናኛ ብዙሃን ለስፖርት የሚሰጡት ሽፋን መጨመርን ተከትሎ፤ ተደራሽነትን ብቻ ሳይሆን ስፖርት ራሱን የቻለ ግዙፍ ዘርፍ እንዲሆን አስችሏል:: ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያም የሚስተዋል ሲሆን ትኩረታቸውን በስፖርት ላይ ያደረጉ የኅትመት፣ የብሮድካስት እንዲሁም ድረ-ገጾች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ ነው:: ለዘርፉ ያላቸው አበርክቶም የላቀ ነው::

ለሀገራት የስፖርት እንቅስቃሴ ማደግ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጽእኖ ፈጣሪ መሆን በስፖርት ሜዳ ላይ የሚመዘገበው ውጤት ብቻውን ዋጋ አይኖረውም:: በመገናኛ ብዙኃን አውታሮች ሽፋን አግኝቶ ለኅብረተሰቡ ተደራሽ መሆን ይኖርበታል:: ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ነባራዊ ሁኔታ እንደሚያሳየው ከሆነም ካሉት የመገናኛ ብዙኃን ብዛት አኳያ በሀገር ውስጥ የስፖርት ጉዳይ ሽፋን በመስጠት የሚሰሩት በጣት የሚቆጠሩት ናቸው:: ስፖርትና መገናኛ ብዙኃን የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሆነው ሳለ የሃገር ውስር ስፖርት ትኩረት ማጣቱ አስገራሚ ቢሆንም፤ ለዚህ የተለያዩ ምክንያቶች ግን ሊነሱ ይችላሉ::

የሀገር ውስጥ ስፖርትን በማስተዋወቅና ታሪክን በመሰነድ ረገድ ከፍተኛውን ሚና ሲጫወት የቆየው የኅትመት ውጤቶች መዳከምና መመናመን ተጠቃሽ ነው:: በስፖርት እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ አተኩረው የሚሰሩ ጋዜጦች በርካታ ቢሆኑም ከኅትመት ዋጋ ውድነት እና በሌሎች ተያያዥ ችግሮች የተነሳ የተዘጉ ጋዜጦች ቁጥር




ጥቂት አይደለም:: በእርግጥ የብሮድካስትና የድረ-ገጾች መፈጠር ለስፖርቱ ትልቅ ትንሳኤን ማምጣት ችሏል:: ነገር ግን በኢትዮጵያ ስፖርቱ በሚገባው ልክ ትኩረት አግኝቶ እንዲያድግ አሰራሮችን በመፈተሽ የተሰራው ስራ አጥጋቢ አይደለም::

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን በስሩ ከሚገኙ ጣቢያዎች ውስጥ አንዱ የሆነውን የኤፍ ኤም አዲስ 97ነጥብ፣ የምስረታ (24 ዓመት) ክብረ በዓልን በተለያዩ ሀገራዊ ጉዳዮች ውይይት በማድረግ ያከበረ ሲሆን፤ ለውይይት ከቀረቡ ጉዳዮች መካከል የስፖርትና የመገናኛ ብዙኃን ግንኙነትን ይመለከታል:: የኢትዮጵያ መገናኛ በዙኃን (ሚዲያ) ለኢትዮጵያ ስፖርት ዕድገት አበርክቶ፣ ተግዳሮቶችና ቀጣይ ጉዞዎች በሚል የመነሻ ሃሳብ ጽሁፎች ቀርበው በስፖርት ጋዜጠኞች፣ የስፖርት ፌዴሬሽን ኃላፊዎች እና አሰልጣኞች ሃሳባቸውን ሰጥተዋል::

በኢትዮጵያ ስፖርት እድገት ውስጥ የኅትመት፣ የብሮድካስትና የበይነ መረብ የመገናኛ ብዙኃን አብረክቶ ትልቅ እንደሆነና ስፖርቱን አንድ እርምጃ ወደ ፊት እንዲጓዝ ማድረጉን በቀረበው ጽሑፍና እና የውይይቱ ተሳታፊዎች ሃሳብ ተነስቷል:: ስፖርቱን በማስተዋወቅ፣ ታሪክን በማነጽ እና በማስተማር ረገድ አስተዋጽኦ አላቸው:: በዓለም መድረክ በስፖርቱ የተፈጠሩ ጀግኖች፣ ድሎች እና ለሀገር የተደረጉ ተጋድሎዎች በጋዜጦች ታትመው፣ በሬዲዮና ቴሌቪዥን ተዘግበው የጋራ ታሪክ በመሆን እንዲዘከሩ ማድረግ ተችሏል:: ኢትዮጵያን በስፖርት በዓለም ደረጃ በውጤታማነት እንድትታወቅና ገጽታዋ እንዲቀየርም አድርገዋል::

ነገር ግን የመገናኛ ብዙኃኑ የዘርፉን አሰራር በመፈተሽ ረገድም መስራት እንደሚኖርባቸውም ነው የተጠቀሰው:: ስፖርት በዓለም አቀፍ የስፖርት ማኅበራት የሚመራ እንደመሆኑ መንግስት የተቋማቱን አሰራር ለመፈተሽ የሚያስችል ኃላፊነት የለውም:: ስለሆነም አሰራሩን በመፈተሽ እንዲስተካከል የማድረጉ መብትና ኃላፊነት የመገናኛ ብዙሃን ይሆናል:: ለዚህም ተገቢውን ትኩረት እና ቦታ በመስጠት የስፖርት ማኅበራትን፣ ክለቦችን፣ ተቋማትን እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ተደራሽ በማድረግ መስራት ይገባል::

የስፖርት ፖሊሲ ማነቆዎች፣ የምርመራ ዘገባ እና የግልጸኝነት ችግር የመገናኛ ብዙሃኑ ለስፖርቱ በትክክል ሽፋን እንዳይሰጡና አሰራራቸውን በተገቢ ሁኔታ እንዳይፈትሹ ተግዳሮቶች የሆኑ ጉዳዮች ተደርገው ተነስተዋል:: አጀንዳ ቀረጻ፣ በቂ ሽፋን፣ የይዘት ጉዳይ እና በተለያዩ አካላት የሚደርሱት ጫናዎችም ስፖርቱ ተገቢውን ትኩረት እንዳያገኝ ከሚያደርጉት ውስጥ ናቸው:: ሚዛናዊነትን ያልጠበቁ ስራዎች፣ አንዳንድ ጋዜጠኞች ሙያው የሚፈልገውን ባህሪ አለመላበስ፣ ሙያ ብቃት ማነስ፣ የስፖርት ባህልን መሸርሸር፣ ... ደግሞ ስፖርቱ እንዳያድግ ማድረጉን ከተሳተፊዎች የተነሱ ነጥቦች ናቸው::

የሃገር ውስጥ ስፖርት ተገቢውን ሽፋን እንዲያገኝና ወደ ፊት ጉዞውን የተሻለ ለማድረግ መስራት ይገባቸዋል በሚልም በተሳታፊዎች የመፍትሄ ሃሳቦች ቀርበዋል:: ከእነዚህ መካከል ለሙያው የሚታመን ጋዜጠኛን መፍጠር፣ ሚዛናዊ ዘገባ፣ አውደ ጥናትና የፓናል ውይይቶችን ማዘጋጀት፣ የመገናኛ ብዙኃን በአዋጅ የተሰጣቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ማድረግ፣ ተጠያቂነት እና ግልጸኝነትን መፍጠር፣ ከሰለጠኑት ሀገራት ጋር የልምድ ልውውጥ በማድረግ ጠቃሚ እውቀቶችን በመቅሰም ስፖርቱን ለማሳደግ ጥረት ማድረግ የሚሉትም ይገኙበታል::


# Specific Procurement Notice

## Request for Bids
## Goods
## (One-Envelope Bidding Process)

**Country:** Federal Democratic Republic of Ethiopia
Name of Project: Ethiopia Flood Management Procurement
**Contract Title:** Procurement of Station Wagons for M&E (Hardtop Field Vehicle)
**Grant No.:E124-ET**
**RFB Reference: ET-EDRMC-397335-GO-RFB**

1.The Federal Democratic Republic of Ethiopia has received financing from the World Bank toward the cost of the Ethiopian Flood Management Project (ETFMP), and intends to apply part of the proceeds toward payments under the contract for the Procurement of Station Wagons for M&E (Hardtop Vehicle) for Ethiopian Disaster Risk management commission (EDRMC).

2. The Ethiopian Disaster Risk Management commission sealed Bids from eligible Bidders for the supply of Station Wagons for M&E (Hardtop Field Vehicle).

| No. | Item | Quantity | Location | Delivery Period |
|---|---|---|---|---|
| 1 | Specification requirement of Station Wagons for M&E (Hardtop Field Vehicle) | 2 Units | Ethiopian Disaster Risk Management Commission (EDRMC) Addis Ababa, Ethiopia | 180 Days |

3.Bidding will be conducted through national competitive procurement using a Request for Bids (RFB) as specified in the World Bank's "Procurement Regulations for IPF Borrowers: Procurement in Investment Project Financing. Goods, Works, Non-consulting and Consulting Services', dated July 1, 2016, revised November 2017 & August 1, 2018; and updated on November 2020 ("Procurement Regulations"), and is open to all eligible Bidders as defined in the Procurement Regulations that meet the following qualification criteria:

4.Interested eligible Bidders may obtain further information from Ethiopian Disaster Risk Management Commission (EDRMC) and inspect the bidding documents at the address given below from 9:00AM to 12:30PM and 2:00PM to 5:00PM local time Monday through Friday

5.The bidding document in English may be purchased by interested Bidders upon the submission of a written application to the address below and upon payment of a Non refundable fee of ETB 500.00 (Five Hundred Ethiopian Birr) or USD 10.00 (Ten United States Dollar). The method of payment will be in cash or direct deposit to EED's account in the Commercial Bank of Ethiopia, Shell Depoe Branch, and EDRMC Account No.1000068658814.Dollar account 0101961300001. The bidding document will be sent by their respective email address or the Bidder can collect the hard copy of the bidding document from the client's address below.

6.Bids must be delivered to the address below on or before 4th July, 2024 at 2:00 P.M. Electronic Bidding will not be permitted. Late Bids will be rejected. Bids will be publicly opened in the presence of the Bidders' designated representatives and anyone who chooses to attend at the address below on 4th July, 2024 at.2:30 PM (immediately after deadline for bid submission).

7.All Bids must be accompanied by a Bid Security of ETB 145,000.00 (One Hundred Forty Five Thousand birr or equivalent.)

8. Attention is drawn to the Procurement Regulations requiring the Borrower to disclose information on the successful Bidder's beneficial ownership, as part of the Contract Award Notice, using the Beneficial Ownership Disclosure Form as included in the bidding document.

9. The address (es) referred to above is (are):

**Ethiopian Flood Management project (ET - FMP)**
**Attention: Mr Haile Assefa P.O. Box: 5686 Addis Ababa, Ethiopia**
**Street Address: Nifas Silk, on the Road from Gotara to Saris, Ethiopian Disaster Risk Management Commission Head Office located next to Nifas Silk Polytechnic Collage Telephone Number: +251-11-406-748**
**Addis Ababa, Ethiopia E-mail address: haile.assefa2023@gmail.com**

## Ethiopian Disaster Risk Management commission (EDRMC)